# ክፍል ሦስት

## አመራርና፥ የኃይልና የሥልጣን ጥያቄ

# ምዕራፍ ስድስት

## የአመራር ዓይነቶችና ደረጃዎች

- *"ለዚህም ነገር የሚበቃ ማን ነው?... በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደተላከን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን።" 2ቆሮ. 2፡16-17)*
- *"ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም።" (2ቆሮ. 3፡5)*

የአመራር ዓይነቶችና ደረጃዎች ማየታችን አስፈላጊ የሚያደርገው ብዙ ምክኒያቶች ቢኖሩም፥ ጥቂቶቹን ለመግለፅ እወዳለሁ። አንደኛ፡- በመሪነት ቦታ ላይ እግዚአብሔር ሲያስቀምጠን የአመራራችንን ዓይነት ጥራቱንና ደረጃውንም ስናውቅ፤ ጉድለታችንን አይተን የበለጠ ለማወቅና ለመለወጥ እንድንናፍቅ ያደርገናል። ካላወቅን ግን እንደምናውቅ ስለሚመስለን ወደከፋ ጥፋትም ሊወስደን ይችላል። ሁለተኛ፡- ምንም እንኳን ያለንበት የመሪነት ደረጃ ማወቃችን ቢያሳምመንም፤ ፈውሱ ግን ዘለቄታ ወዳለው የጸጋ እርከን እንድናድግና እንድንለወጥ ያደርገናል። ሦስተኛ፡-የመሪነት ደረጃችንን ማወቅ እኛም ገና ያልተለወጥንባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ስለምናስተውልና ተሠርተን እንዳላለቅን ስለምንገነዘብ፤ የምናገለግላቸው ሰዎችም ይሁን አብረውን የሚያገለግሉት ሌሎች አገልጋዮችን ለመረዳት አንቸገርም። አራተኛ፡-የመሪነት ደረጃችንን ማየት በብርታታችን ጌታን ለማመስገን፤ በጉድለታችን ደግሞ በጌታ ለመሠራት ልባችንን እንድንከፍት ያደርገናል።

የአመራር አይነቶችና ደረጃዎችን ለማየት እንዲያመች አራት ዓይነት መሪዎች እንዳሉ መግለጹ በጣም ይረዳል ብዬ አምናለሁ። እነዚህ የመሪዎች ዓይነትና ደረጃቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

- ያልበቁ ነገር ግን አለመብቃታቸውን ያላወቁ፤
- ያልበቁ፤ ደግሞም አለመብቃታቸውን ያወቁ፤

❖ የበቁ ደግሞም መብቃታቸውን ያወቁ፣ እና

❖ የበቁ ነገር ግን መብቃታቸውን ያላወቁ ናቸው::

የእነዚህንም የመሪዎች ዓይነት ብርታትና ድካም ተራ በተራ እንመለከታለን::

## I. የአመራር ዓይነቶችና ደረጃዎች

### ሀ. "ያልበቁ፥ ነገር ግን አለመብቃታቸውን ያላወቁ፣"

### ("UNCONCIOUS, INCOMPETENT")

ጌታ ኢየሱስ "*በመንገድ ዳር ወደቀ፣ ወፎችም መጥተው በሉት*" (ማቴ. 13:4) ያለው ከፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና ጸሐፍትን የሚመሳሰል ነገር አለው::

እንደዚህ ዓይነት መሪዎች ለመሪነት የሚያበቃ ብቃት የላቸውም:: በጣም የሚገርመው ደግሞ የማይበቁ መሆናቸውንም አያውቁም:: የአመራር እውቀቱም ይሁን ችሎታው የላቸውም:: በውስጣቸው ያለው እርግጠኝነት ካላቸው አቅምና የአመራር ችሎታ ጋር አይመጣጠንም::

1. ብርታታቸው:-

- ✓ የማይደክም ኃይልና ጉልበት አላቸው:: ተናግረው፣ አገልግለው፣ ተሰብስበው ሮጠው ወዘተ አይደክሙም::
- ✓ ከሚገባ በላይ የተለጠጠ የእግዚአብሔር ቤት ቅንዓት አላቸው::
- ✓ በአንድ ጊዜ ብዙ ነገሮችን ማቀድ፣ ሐሳቦችን ማፍለቅ፣ ፍላጎታቸውን መግለፅ ይችላሉ::
- ✓ እንደህ ዓይነት መሪዎች ገና በማደግ ላይ ያሉ ስለሆኑ በብዙ ጥበብና ማስተዋል ሊያዙ ይገባቸዋል:: (መዝ 127:4)

2. ድካማቸው:-

- ➢ ከሚገባ በላይ ደፋሮች ስለሆኑ በቤተ ክርስትያን ውስጥ አላስፈላጊ የሆነ ጭንቅንቆሽና ውጥረት ያመጣሉ::
- ➢ ሁልጊዜ አሠራራቸው በጥድፊያና በችኮላ ስለሚደረግ አፍራሽ የሆነ ተጽዕኖ አለው::

- ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ብዙ እንደሚያውቁ ይመስላቸዋል።
- ከቆዩና ነባር ከሆኑ መሪዎችና አገልጋዮች ምክር ለመጠየቅ አይፈልጉም።
- ከእነርሱ በላይ በተቀመጡ መሪዎች ላይ ትችትና ሐሜት ያበዛሉ።
- ቤተ ክርስቲያን እንድትከፋፈል የሚያደርግ ቅስቀሳ ያካሂዳሉ።
- ጥበብ በጎደለውና ወቅቱ ባልጠበቀ መንገድ በራሳቸው ላይ አላስፈላጊ የሆነ ቁስል የሚያመጣ ዋጋ ይከፍላሉ።

## ለ. "ያልበቁ፥ ቢሆንም አለመብቃታቸውን ያወቁ ("CONCIOUS, INCOMPETENT")

እንዲህ ዓይነት መሪዎች አለማወቃቸውን ያወቁ፣ የማይበቁ መሆናቸውን የተገነዘቡና ማደግና መለወጥ ያለበት በርካታ የአመራር ድካሞች እንዳላቸው የተገነዘቡ ናቸው። ክፋቱ ግን የራሳቸውን ውስንነት በገባቸው መጠን የነበራቸው እርግጠኝነት እያሽቆለቆለ ይመጣና ለምንም ነገር የማይበቁ ይመስላቸዋል። ከዚህም የተነሣ ዘመናቸውን በማጉረምረምና ስለ ራሳቸው በማቁዘምዘም የማሳለፍ ዝንባሌ አላቸው። ከእነርሱ የተሻሉ መሪዎች ሲያዩ ራሳቸውን በማይመች አቀማመጥ ያስቀምጣሉ። እነዚህ ጌታ ኢየሱስ "*ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፣ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረውም ደረቀ።*" እንዳለው ብዙኃኑ ሕዝብ ይመስላሉ።

1. ብርታታቸው:-

- ✓ ከመጠን ያለፈ "ትሑታን" ናቸው። ትሕትናቸው ግን በመከራ የተቀመመ፣ በጌታ በመለወጥ የመጣ ሳይሆን "አልበቃም" ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።
- ✓ ለመማር፣ ለማወቅና ለመስማት ፈቃደኞች ናቸው።
- ✓ ለሌሎች መሪዎችም ይሁን ምዕመን ምክር ክፍት ናቸው።
- ✓ የፉክክርና የውድድር መንፈስ አይታይባቸውም።
- ✓ የግል አጀንዳም ይሁን ወይንም ለሥልጣንና ለኃይል የሚቋምጥ ልብ የላቸውም።

2. ድካማቸው:-

- "አልበቃም፣ አልችልም" በሚል ስሜት የተሞሉ ስለሆኑ በራስ ማቁዘምዘም የተሞሉ ናቸው።
- በቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸውን የአገልግሎት ዕድል ለመቀበል ይሳናቸዋል።

- በግል ሕይወታቸውም ይሁን በአገልግሎታቸው ለማደግ ምንም ዓይነት ዕቅድ የላቸውም::
- በራስ ማቁዘምዘም የተዋጡ ስለሆኑ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ዕዳሎት የተሞላ በት ዘመን (በግሪክ "KAIROS") ከእጃቸው ያመልጣል::
- እውነትን ማመቻመች፥ መሸራረፍና፥ መቀያየጥ ይወዳሉ::

## ሐ. "የበቀ፥ መብቃታቸውን ደግሞ የሚያውቁ፤" ("CONCIOUS, COMPETENT")

ጌታ ኢየሱስ "*ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾህም መጣና አነቀው::*" (ማቴ. 13:7) እንዳለው፤ ካለ የጌታ እናት ማርያም በስተቀር የጌታ ቤተሰብ ይመስላሉ:: እንዲህ ዓይነት መሪዎች የበቁ ናቸው፤ መብቃታቸውን ደግሞ ከሚገባ በላይ ያውቃሉ:: የአመራር ቦታ፤ የእግዚአብሔር ፀጋ ሹመትና ስያሜ ለእነርሱ እንደሚገባ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው:: ከዚህ ሁኔታቸው የተነሣ እስከ አሁን ካየናቸው ሁለቱ መሪዎች ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን በብዙ ሊጎዱ የሚችሉ ናቸው::

1. ብርታታቸው:-

- ✓ የተጠራቀመና የታጨቀ እውቀት አላቸው::
- ✓ ስለ እግዚአብሔር ብዙ ያውቃሉ፤ እግዚአብሔር ራሱን የሚያውቁት እውቀታቸው የተመጠነ ቢሆንም::
- ✓ ለመምራት ሁልጊዜ ፈቃደኞችና ዝግጁዎች ናቸው፤ እንዲያውም ባይመሩ ነው የሚገርማቸው::
- ✓ የአደባባይ ወይም የመድረክ አገልግሎት ብቻ ይቀናቸዋል፤ የማይታይ አገልግሎት አይወዱም:: (ይኸ ብርታታቸውም ድካማቸውም ነው::)
- ✓ በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ናቸው::

2. ድካማቸው:-

- የአዕምሮ እውቀታቸው ብዙ ቢሆንም፤ የልምምድ እውቀታቸው ግን በጣም የተመጠን ነው::
- የግል/ የጓዳ ኑሮአቸው ከአደባባይ አገልግሎታቸው ጋር ሁልጊዜ ይቃረናል፤ አይስማማም::

- ዝነኛ ለመሆን በጣም ይፈልጋሉ፤ ከዚህ የተነሣ ዘመናቸውን ስለ ስማቸውና ስለ ተቀመጡበት ሥፍራ ሲሟገቱ፤ ለመጠበቅም ሲታገሉ ያሳልፋሉ።
- በብዙ ሥፍራና ስብሰባ የተወጠሩ ናቸው፤ በብዙዎች ዘንድ ይታወቃሉ፤ በሕዝብ ፍላጐት የተመሩ መሪዎች ናቸው። ሆኖም በሰዎች ላይ የሚያመጡት ለውጥ ግን የለም፤ ካለም ትንሽ ነው።
- ከሌሎች መሪዎችም ይሁን ከሕዝቡ ምንም ዓይነት ምክር፤ ሐሳብ ምሪት ሊቀበሉ አይፈልጉም።
- እጃቸው ያልገባበት ኮሚቴ፤ ቦርድ ወይም ቡድን የለም፤ በሁሉ ሥፍራ የተበተኑ ፤ ያልሰከኑና፤ ቅደም ተከተላቸውን የማያውቁ፤ ወይም የዛሉ ናቸው።
- በሌሎች መሪዎች ሥር መቀመጥ፤ በሌላ መሪ መመራትም አይወዱም።
- ቤተ ክርስቲያን ያለነርሱ ትክሻ (አመራር፤ እውቀት፤ ገንዘብ፤ ሐሳብ) መቆም የምትችል አይመስላቸውም። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗ ቀርቶ የራሳቸው እንደሆነች ለመናገርም አያፍሩም። ከዚህ የተነሳ ከተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ይመስላሉ። (1ቆሮ. 1፡2 VS 1ተሰ. 1፡1)

## መ. "የበቁ÷ የበቁ መሆናቸውን ግን ያላወቁ፤"

## ("UNCONSCIOUS, COMPETENT")

ጌታ ኢየሱስ "*ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ ወጥቶ አድጎ ፍሬ ሰጠ፤ አንዱም ሠላሳ፤ አንዱም ስድሳ አንዱም መቶ አፈራ።*" (ማር 4፡8) የተባለላቸው አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርትን የሚመስሉ ናቸው።

<u>እንዲህ ዓይነት መሪዎች የበቁ፤ የነጠሩና የበሰሉ መሪዎች ናቸው፤ ነገር ግን እንዳልደረሱበት ብቻ ስለሚያውቁ ጌታን የመምሰል ናፍቆታቸው የማያቋርጥ ነው።</u> ሐዋያው ጳውሎስ፦ " ወንድሞች ሆይ፤ እኔ ገና እንዳልያዝኩት እቆጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፤ ....." (ፊል. 3፡13-14) እንዳለው ለመለወጥ፤ ለማደግ፤ "እርሱን.... እንዳውቅ ....እመኛለሁ።" (ፊል. 3፡10-11) እንዳለው ጌታን ለማወቅ የእግዚአብሔርን ፊት ከመፈለግ የማያቆሙ መሪዎች ናቸው። የእነዚህ መሪዎች አጀንዳ አንድ ነው! (መዝ 27፡4፥8፤ ፊል. 3፡10-11፤ 13-14፤ ሉቃስ 10፡42) ድካም የላቸውም ማለት አይደለም፤ ድካማቸው እየበዛ ከሄደ ግን ወደኋሊት ይመለሳሉ።

❖ የማይታይ፣ ሥውር አገልግሎት ይቀናቸዋል:: እንዲያውም እነዚህ መሪዎች"<u>እየ ታዩ የማይታዩ መሪዎች</u>" (VISIBLE INVISIBLE LEADERS) ናቸው::

❖ ሌሎች መሪዎችን ለማጎልበት (MENTORING)፥ ለማበረታታትና፥ ለመደገፍ ልዩ ጊዜያቶችን ይሰጣሉ::

❖ ላለመምራትም ፈቃደኛ ናቸው:: ሌሎች ሲመሩና አዳዲስ መሪዎችም ሲነሡ ደስ ይላቸዋል፣ ክብራቸው ነው!

❖ የግል አጀንዳ የሌላቸውና ለሥልጣንና ለኃይል ሲታገሉ የማይታዩ ናቸው::

❖ በዘመናት መካከል የተፈተነና የነጠረ ጥበብና እውቀት አላቸው::

❖ በመንፈሳዊ አመራራቸው እጅግ የበሰሉ ቢሆኑም፣ ለሌሎች ሰዎች ሐሳብ፣ ምክ ርና አመራር የተከፈተ ልብ አላቸው::

❖ ሰውን ሁሉ እንደ ዕድሜውና (ግልገሉን፣ ጠቦቱንና በጉን)፣ እንደየ ክርስትና እድገቱ መጠን ሳያዳፉት ማሳደግ የሚችሉበት ጥበብ አላቸው::

❖ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያሰፋል ብለው ባመኑበት ጉዳይ የመወሰን ችሎታ ቸው ከፍተኛ ነው::

❖ ስለ ወንጌል ጥሪና ስለ ተጠሩለትም ሕዝብ ሕይወታቸውን መስዋዕት ከማድረግ ወደ ኋላ አይሉም::

❖ አስተውሎ ለሚያያቸው ሰው አስገራሚ የሆነ የማያቋርጥ ለውጥ በሕይወታቸው ም ይሁን፥ በአገልግሎታቸው ስለሚታይ የሚያስቀኑ ናቸው::

❖ የእግዚአብሔርን ክብር ላለመሻማት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ::

❖ ሰዎችን ለመሳብ ምንም ዓይነት ጥረት አያደርጉም:: ተከታይ እንዲኖራቸውም በፍፁም አይፈልጉም:: የከበሬታ ወንበር የሰው ጎብታና የሕዝብ ጭብጨባ ፈላጊ ዎች አይደሉም::

❖ በጣም የሚገርመው ግን በሁሉ ዘንድ ተፈላጊና ተወዳጅ ን ናቸው፣ እነርሱ ሳያ ውቁት በብዙዎች ዘንድ ሞዴል መሪዎች ተደርገው የተወሰዱ ናቸው::

❖ ከሰው ጋር አብሮ ለማልቀስም ይሁን፣ ደስ ከሚላቸው ጋር ደግሞ ሐሴት ለማድ ረግ የሚችሉበት ብስለቱ አላቸው::

❖ የእግዚአብሔርን ልብ የሰበረ ነገር ሁልጊዜ ልባቸውን ይሰብራል:: ኃጢያትንና አመጽን ለመጋፈጥ የሚችሉበት ልዩ ፅናትና ድፍረት አላቸው::

❖ በአገልግሎታቸው ዘመን ከብዛት ይልቅ ጥራት ላይ ያተኩራሉ!!!

2. አብዛኛው የእግዚአብሔር ትልልቅ ሥራ የተሠራው በሚታዩ መሪዎች ሳይሆን በማይታዩት ነው!!!

❖ በሙሴ ሳይሆን፤ የሙሴ አማች በነበረው በዮትሮ፤ ለአርባ ዓመታት ሙሉ ሙሴን በምድረ-በዳ ከመምከሩም ሌላ፤ በአመራር ላይ ሲቀመጥም ዮትሮ የሙሴ አገልግሎት እንዳይበላሽ ምክሩን ቀጥሏል:: (ዘፀ. 18:1-27)

❖ በኢያሱ ሳይሆን፤ "ልዩ መንፈስ በነበረው በካሌብ፤" (ዘኍ. 14:24፤ 13:1-33፤ 14:1-10፤ ኢያሱ 14:7-15፤ 15:13-19)

❖ በሐዋርያው ጳውሎስ ሳይሆን፤ እየታየ በማይታይ መሪ በበርናባስ፤ በርናባስ በመስዋዕትነት ዋጋ ከፍሎ ጳውሎስን ከሐዋርያት ጋር ያስተዋወቀው እርሱ ነው:: (የሐዋ. ሥራ 9:26-30)

❖ በርናባስ በአንፆኪያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለማምጣቱ ምክኒያት ቢሆንም ጳውሎስ ለአህዛብ መጠራቱን አውቆ ወደ አንፆኪያ አምጥቶ ከተጠራበት ጥሪ ጋር ያገናኘውም እርሱ ነው:: (የሐዋ. ሥራ 11:19-26) ጳውሎስንም በሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ እንዲያድግ የረዳው በርናባስ ነው:: በርናባስ ለጳውሎስ ብቻ  ሳይሆን ለሐዋርያትም ሁሉ " የመጽናናት  ልጅ" እስኪሉት ድረስ ልዩ በረከት ነበር:: (የሐዋ. ሥራ 4÷ 36)

❖ ታናሽ በነበረው በማርቆስ ሳይሆን፤ በእርሱ ተስፋ ሳይቆርጥ ወስዶ ያሳደገው፤ "የሚጠቅም አገልጋይ" እንዲሆን የረዳውና የመጀመሪያውንም የታመነ  ወንጌል የማርቆስ ወንጌል እንዲፅፍ ያበቃው በርናባስ ነው:: (የሐዋ. ሥራ  15: 36-41 ፤ 2ጢሞ. 4: 11፤ ማር. 1÷ 1)

❖ በመናገር ችሎታው ምስያ የሌለው÷ የማጠጣት አገልግሎት የነበረውና ሉቃስም "ነገር አዋቂ" ያለው÷ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንም ባመለከችው በአጵሎስ ሳይሆን፤ አንድ ቀንም ሰብከው በማያውቁ÷ እየታዩ በማይታዩ÷ በስውር ሰዎችን ማገልገል የሚችለውን አጵሎስን ያሳደጉና ለቁም ነገር ያበቁ÷ ከስህተትም  እንዲጠበቅ እውነትን ከፊት ይልቅ የገለፁለት ባልና ሚስት በነበሩት ጵርስቅላና አቂላ ትልቅ÷ ክቡርና÷ ልዩ ሥራ ተሠርቶ እናየዋለን:: (የሐ. ሥራ 18:24-28)

- ቁጥር 1፤ በቁጥር 4 ላይ ትዕግሥት የላቸውም::
- ቁጥር 2፤ የቁጥር 1 እና የቁጥር 3 መጠቀሚያ ናቸው::
- የሕይወታችንና የአገልግሎታችን ናፍቆት ቁጥር አራትን ለመምሰል እንዲሆን እመክራልሁ!!!

## II. "በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አመራር" (SITUATIONAL LEADERSHIP)

የአመራር ዓይነቶችና ደረጃዎች በተመለከተ እስከ አሁን የተመለከትኳቸውና ነገሩን የበለጠ ትኩረት ሰጥተን ለማጤን ይረዳናል ብዬ እላይ አቅርቤአቸዋልሁ:: አሁን ደግሞ ፓውል ሄርሰይ፤ ኬኔዝ ብላንቻርድና ዴዊ ጆንሰን የሚባሉ ጸሐፊዎች ከጻፉት መጽሐፋቸው[75] ውስጥ "በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አመራር" (SITUATIONAL LEADERSHIP) የሚለውን አንዱ ምዕራፍ ሊገባን በሚችል መልኩ ጨምቁ ለማቅረብ እሞክራለሁ:: በመጀመሪያ የምዕመኑ የሕይወት መሰጠት ደረጃ ካየን በኋላ፥ በመቀጠልም ለእንዲህ ዓይነት ምዕመን ምን ዓይነት መሪ እንደሚያስፈልግ ጸሐፊዎቹ ያቀረቡትን አቀርባለሁ:: ይህ መጽሐፋቸው ብዙ እንድናስብ ስለሚያደርገንና ምናልባት ማየት ካለብን ነገሮች መካከልም ስለሆነ እንጂ፤ የዚህ መጽሐፍ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ አምኜበታለሁ ማለት አይደለም::

---

[75] Paul Hersey, Kenneth H. Blanchard, and Dewey E. Johnson, Managemenet of Organizational Behaviour, 7th. ed., (upper Saddle River, NJ: Prentice Hall, 1996), 188-227.

ሀ. የምዕመን ዝግጁነት ደረጃ፡-

1. “የማይችሉና ፈቃደኛ ያልሆኑ ወይም ፍርሃት ያላቸው”

እንዲህ ዓይነት ምዕመን ችሎታውም የላቸውም፣ ወይም የተሰጣቸውን ሥራ ለመፈፀም ፈቃደኝነት የላቸውም። በራሳቸው መተማመን የማይችሉና ሥራውን ለመፈፀም እንደሚችሉ አያምኑም። ከዚህ የተነሣ የሆነ ያልሆነ ምክኒያቶችን በመስጠት ከኃላፊነት መሸሽ የሚወዱ ስለሆኑ፣ ጠንካራ አመራር ያለው መሪ ያስፈል ጋቸዋል።

❖ መሪው ሕዝቡን የሚያነሣሣው አገልግሎት በመስጠት፣ የተወሰኑ ትዕዛዞችንም በመስጠት፣ በፐላን፣ በሥራ በማዋልና በግምገማ፣ በቅርብ ሆኖ ሊረዳቸው ይገባል

2. “የማይችሉና ፈቃደኞች፣ ወይም እርግጠኝነት ያላቸው፣”

እንዲህ ዓይነት ምዕመን በራሳቸውም ሆነ በሚያደርጉት ነገር ሥራውን ለመ ሥራት እርግጠኝነት ስላላቸው የተሰጣቸውን ሥራ ለመፈፀም ይችላሉ። እንዲያው ም የተለየ ደስታና መነቃቃት አላቸው። የሚመራቸውና የሚያስተምራቸው መሪ ካገኙ የሚቀበልና ምላሽ የሚሰጥ ልብ አላቸው። ነገር ግን ችሎታና እውቀት ስለሚጎድላቸው በዚህ እጃቸው ይያዛል።

❖ መሪው ለማነሳሳት ከመሞከር ይልቅ፣ ሊሠራ የተፈለገውን ነገር እንዴት መደረ ግ እንዳለበት ሐሳብ፣ ትምህርትና ምሪት ቢሰጣቸው የበለጠ በመስጠት ሊሠሩ ይችላሉ።

3. “የሚችሉ፣ ነገር ግን ፈቃደኝነት የሌላቸው ወይም እርግጠኝነት የሚጎድላቸው፣”

እንዲህ ዓይነት ምዕመን ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውና የተሰጣቸውንም ሥራ በሚገባ ለመፈፀም የሚችሉ ናቸው፣ ምንም እንኳን አንዳንዴ ችሎታቸውን ቢጠራ ጠሩትም። አልፎ አልፎ ከመጠን በላይ ኃላፊነት ስለሚሰማቸው ሸክሙ ያጎብጣቸው ና ቀጣይነት ያለው ፈቃደኝነት ይጎድላቸዋል፣ እርግጠኝነትም የላቸውም።

4. "የሚችሉ፣ ፈቃደኝነትና እርግጠኝነት ያላቸው፣"

እንዲህ ዓይነት ምዕመን ከፍተኛ ችሎታ፣ ፈቃደኝነትና እርግጠኝነት ያላቸው ስለሆኑ:: የተሰጣቸውን ሥራ በትጋት፣ በመሰጠትና በሙሉ ፈቃድና ደስታ የሚፈፅሙ ናቸው:: በአገልግሎት ሲሠማሩም  የሚያደርጉትን የሚያውቁ ብቻ ሳይሆን፣ ልብን በሚያረካ መልክ የጠራ ሥራ መሥራት የሚችሉ ናቸው:: መሪው እንደ ወላጅ ሊመራ ሲፈልግ አይጥማቸውም:: ከመሪው ብዙ ትምህርትና ምሪት ሲሰጣቸው በቀላሉ ይሰለቻቸዋል::

- ❖ መሪው ሆነ ብሎ ኃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ ውሳኔ ሲወስኑም ሊታመንባቸው ይገባል::

### ለ. የአመራር ዓይነቶች:-

1. "ትዕዛዝ ሰጪ መሪ":- ("TELLING LEADER")

እንዲህ ዓይነት መሪ በሚሠራው ሥራ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያለው ሆኖ፣ ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ግን በጣም አነሥተኛ ነው:: ከምዕመኑ ጋር ካለው የግንኙነት ጥምረት ይልቅ፣ በሚሠራው ሥራ ላይ ስለሚያተኩር ዝርዝር ትዕዛዞችን በመስጠት ይመራል:: ይህ ዓይነት መሪ "የማይችሉና ፈቃደኝነት ወይም እርግጠኝነት የሌላቸው "ምዕመን ለመምራት ይመቻል::

- ❖ የዚህ መሪ ድካም ግን ከሕዝቡ ጋር ያለው የግንኙነት ሥምረት እየዳበረ እንዲሄድ ከማድረግ ይልቅ፣ "ትዕዛዝ ሰጪ" ብቻ ከሆነ ሕዝቡ ያለ አቅሙ እንዲወጠር፣ ሕዝቡን አለ አግባብ የሚጫን፣ ደግሞ የሚንቅና አልፎም የሚሳደብ ይሆንና የተጠራለትን ሕዝብ ይረግጣል::

2. "ሐሳቡን ወይም ራዕዩን የሚሸጥ መሪ":-
("SELLING LEADER")

እንዲህ ዓይነት መሪ በሚሠራው ሥራና በግንኙነት ጥምረት ላይ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ያለው መሪ ነው:: መሪው ለሚመራቸው ምዕመን የተወሰነውን ውሳኔ በማስረዳትና ግልፅ ያልሆኑላቸው ጉዳዮችም በማብራራት ላይ ያተኩራል:: ማን? የት?

መቼ? ምን? እንዴት ለምን? እና ውጤቱ? ለሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ብቃት ያላቸው መልሶች ይሰጣል።

- ❖ እንዲህ ዓይነት መሪ ሕዝቡን በማነሣሣትና በማበረታታት ላይ በማተኮር የሕዝቡን ሞራል አነሣስቶ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ያደርጋቸዋል።

3. **"የሚያሳትፍ መሪ"**:- ("PARTICIPATING LEADER")

እንዲህ ዓይነት መሪ ከሚመራው ሕዝብ ጋር የተጠበቀ የግንኙነት ሥምረት ያለው ሆኖ፣ ሊሠራ ለሚገባው ሥራ ግን ዝቅተኛ ትኩረት የሚሰጥ መሪ ነው። የሚመራውን ሕዝብ በማቀድ፣ በሥራ በመተርጎምና በግምገማ እንዲሳተፍ ያደርገዋል። መሪው ሕዝቡን ሳይጫንና ሳያስገድድ ሐሳቡን እንዲካፈሉ ያደርጋል። ውሳኔ የመስጠት ሂደት እንዲካሄድና እንዲካፈሉም ያደርጋል።

- ❖ መሪው በሚመራው ሕዝብ ላይ እምነትና እርግጠኝነት ፍላጎትም ያለው ከመሆኑም ሌላ ያላቸው እምቅ ችሎታ እና እውቀት ጠንቅቆ ያውቃል። ሕዝቡን በውሣኔ አሰጣጥም ሆነ በሥራ ላይ በማዋል እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል።

4. **"የሚወክል መሪ"** ("DELEGATING LEADER")

እንዲህ ዓይነት መሪ ከሚመራው ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ ጤናማ ቢሆንም፣ በጣም የጠበቀ እንዳይሆን ግን ይፈልጋል። በዚያው መጠን መሠራት ያለበትም ነገር፣ በሕዝቡና በሌሎች አገልጋዮች ካለው እምነት የተነሣ በውክልና እያገለገሉ ማየት ደስታው ስለሆነ "ሥራው ላይ ብቻ" የተለየ ትኩረት የለውም። የሕዝቡ እምቅ ስጦታና ችሎታ አጥልቆ ያውቃል፣ የጠራ ሥራ እንደሚሠሩም ያምናል።

- ❖ መሪው ሕዝቡ ዕቅድ በማውጣት፣ በማስፈፀምና በግምገማ ሙሉ በሙሉ (ያለ ምንም መቆጠብ) እንዲሳተፉ ያደርጋል። የእርሱ ድርሻ አጠቃላይ ስዕሉን ማየትና ዓላማውን መምታቱን፣ የታሪክ አቅጣጫ ሂደት ማንበብና መተርጎም፣ እና የሕዝቡ እምቅ ስጦታ ተፈልቅቆ መውጣቱን ማየት ነው።

# ምዕራፍ ሰባት

## አመራር:- የሥልጣንና የኃይል አጠቃቀም

- *"ኢየሱስ ግን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው የአህዛብ አለቆች እንዲገዙ አቸው፥ ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ:: በእናንተስ እንዲህ አይደለም:: ((ማቴ. 20:25)*
- *"ጌታ እናንተን ለማነፅ እንጂ እናንተን ለማፍረስ ያይደለ በሰጠው በሥልጣ ናችን..." (2ቆሮ. 10:8)*
- *"ስለዚህ ጌታ ለማፍረስ ያይደለ ለማነፅ እንደ ሰጠኝ ሥልጣን...እጽፋለሁ::" (2ቆሮ. 13:10)*

### I. መግቢያ:-

በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያንም ይሁን፣ ቤተ ክርስቲያን አገዝ በሆኑ መንፈሳ ዊ ድርጅቶች በአመራር ላይ የተቀመጡ አንዳንድ መሪዎች ስለ ሥልጣንና ኃይል አጠቃቀም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳት እንደሚጎድላቸው ከሚያሳዩአቸ ው ሕብረ-ብዙ ባሕርያት ለማየት አያዳግተንም:: ከእግዚአብሔር ቃል እይታ አንጻ ር የሥልጣንና ኃይል ትርጉመ ወሰን ካለማወቅና፣ ኃይልና ሥልጣን አለ አግባብ መጠቀም የሚያመጣውን ሰበብ ካለማስተዋል የሚመጣ ይመስለኛል:: ሌላው ደግሞ እግዚአብሔር የሥልጣንና የኃይል ምንጭ ብቻ ሳይሆን ባለቤትም እንደሆነና መሪ ዎቹ ባለ አደራ ብቻ መሆናቸውን ባለመገንዘብና፣ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ምንነት ወይም ባሕርይ ባለመረዳት እንደማናቸውም ድርጅት እንደምት ተዳደር እንደምትደረግ በማሰብ የሚመጣ ሊሆን ይችላል:: አንዳንዱም "አምላክ ለመሆንና ለመመለክ" ከመፈለግ የተነሣ ከጌታ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ኃይል

የእግዚአብሔርን መንፈስ በሚያሳዝን መልክ ሲጠቀሙበት የሚመጣ ጉዳይ ነው:: ይህ ሁሉ አስተዋይ ለሆነ ሰው እጅግ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው:: የሐርቨርድና የየል ዩኒቨሲቲዎች ውስጥ ለረዥም ዓመታት ፕሮፌሰር ሆኖ ሲያስተመር የነበረው ሄንሪ ኑወን የሚባለው የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ ብሎ ጽፏል፡-

"ኃይልን በተመለከተ ያለው ፈተና ልንቋቋመው የማንችለው ነገር ለምን ያደር ገዋል? ምናልባትም ጠንካራ ሥራና ውሳኔ የሚጠይቀውን ፍቅርን ስለመግለፅ ቀላሉ መንገድ ኃይል መጠቀም ስለሆነ ነው:: እግዚአብሔርን ከመውደድ ይልቅ፣ እግዚአ ብሔር መሆን ይቀላል፤ ሕይወትን ከመውደድና ከማድነቅ ይልቅ፣ ሕይወትን በንብረ ትነት መያዝ ይቀላል:: የግንኙነት ጥምረት ወይም ሥምረት የሚያስፈራራ በሚሆን በት ጊዜ፤ ኃይልን አለ አግባብ መጠቀም ፈተናው የላቀ ይሆናል::"[76]

በጣም አስቸጋሪው ጥያቄና ያለው ተግዳሮት በሥልጣንና በኃይል ላይ ከተመሠረተ አመራር ወጥተን፣ እግዚአብሔር ወደ ጠራን የአገልጋይ መሪነት መንፈስ እንዴት ልንመለስ እንችላለን? የሚለው ነው::

እግዚአብሔር የጠራቸውን መሪዎች ለመጠበቅ ሲል በራሳቸውና በራሳቸው መካከል፤ እነርሱን ከራሳቸው ለማዳን ሲል "የጸጋ ግርዶሽ ወይም ግድግዳ" አድርጓ ል:: ይህ የጸጋ ግርዶሽ ግን መሪው በአገልግሎቱ ታዋቂና ዝነኛ እየሆነ በመጣ ቁጥር እየተሸረሸረ መምጣቱ አይቀሬ ነው:: ምክኒያቱም መሪው የሕዝብ ሆታ፥ ጭብጨባ ና ምስጋና በበዛለት ቁጥር፤ አይቶት በማያውቀው መንገድ ራሱን ማየት ይጀምርና ይጣፍጠዋል:: ራሱንም ማምለክ ስለሚጥመው እግዚአብሔር በላዩና በዙሪያው አርጎ ለት የነበረውን መጠበቂያ "የጸጋ ግርዶሽ" ሊሰብረው ይጀምራል፤"የራሱንም ነፃነት" ያውጃል:: እንዲህ ማድረግ በቀጠለ ቁጥር ሥልጣንና ኃይል መጠቀም ስለሚጥመው ፍርሃት ፍርሃት ይለዋል:: ስለዚህም ሥልጣኑንና ኃይሉን ያለ አግባብ በመጠቀም በተጠራለት ሕዝብ ላይ ከማገልገል ይልቅ ሊገለገል፣ ከማነጽ ይልቅ ሊያፈርስ፣ ከሚ ጠቅም ይልቅ መጠቀሚያ ሊያደርግ፣ ከማጎልበት ይልቅ ሊያናንቅና ሊያሳንስ፤ ጸጋ ከሚጨምር ይልቅ ሊጫን ይጀምራል:: እዚህ ደረጃ ላይ በሚደርስበት ጊዜ እግዚአ ብሔር "በመጥራቱ ስለማይፀፀት" (ሮሜ፥ 11:29) በጠራቸው ሰዎች ላይ ምንም ጊዜም ቢሆን ከባድ በሆነ ፍርድ በመሪው ላይ ባይመጣም፤ እግዚአብሔር እጁንና

[76] Henri J.M. Nouwen, In the Name of Jesus: Reflections on Christian Leadership (New York: Crossroad, 1995), 59-60.

ጸጋውን ግን ከላዩ ያነሳና ብቻውን ይተወዋል። አብሮነቱም ከእርሱ ጋር እንዳይቆም ይከለክላል። በዮሐንስ 10፡ 22-23 ላይ *መሪዎቹ፥* (*ማለትም ፈሪሳውያን፣ ጸሐፍትና* ሰዱቃውያን ) ሊያመልኩ በቤተ መቅደስ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ "***ኢየሱስም በመቅደ ስ በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ይመላለስ ነበር።***" እንደሚለው፣ ጌታ ኢየሱስ ከመሪው ጋር ራሱን ማመሳሰል፥ ወይንም አብሮ መቆም ይሳነዋል። የእግዚአብሔር ፊትና እጅ እንደዚሁ በመሪው ላይ ሲከብድ በጣም አስጨናቂ ነገር ነው ብዬ አስባለሁ።

ይህንን ከዚህ በላይ የገለጽኩትን ክብዮሽ እንዴት እንበጥሰዋለን? የእግዚአብሔር ጸጋ በላያችን እንደ ተጠበቀ ለማቆየት ምን ማድረግ አለብን? ራሳችንን ለማምለክም ሆነ፣ ሌሎች እንዲያመልኩን ከመፈለግ ለመታገድ ምን እርምጃዎች መውሰድ ይኖርብናል? የሥልጣንና የኃይል ትርጉመ ወሰን ምንድ ነው? የተቀመጥንበት የመሪነት ወንበር ምክኒያት የመጣ ኃይልና መካከልና፣ በሕይወት ምሳሌነት የመነጨ ሥልጣንና ኃይል መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው? የኃይል ዓይነቶች ምንድ ናቸው? የሥልጣንና የኃይል አጠቃቀም የለውጥ ሂደት ዕድገቶች አሉን? የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሥልጣንና ኃይል ምንነትና አጠቃቀም ምን ይላል?

## II. ትርጉመ ወሰን:-

### ሀ. የኃይል ትርጉመ ወሰን:-

"ኃይል" የሚለው ቃል የመነጨው ከላቲን ቋንቋ "ፖቴር" ከሚለው ቃል ሲሆን ፣ ትርጉሙም "አንድን ነገር ለማድረግ የመቻል አቅም"[77] ማለት ነው። ሌሎች ጸሐፊዎች ደግሞ "በሌሎች ሰዎች ላይ ተፅዕኖ ማምጣት"[78] ብለው ተርጉመውታል። ጆን ቢ ማይነር የሚባለው ፀሐፊ ደግሞ "አንድን ሰው ለማድረግ የማይፈልገውን እን ዲያደርግ ለማስገደድ መቻል ነው"[79] ይለዋል። ከዚህም በመቀጠል ጆን ማይነር "ተፅዕኖ ማምጣት የሚለው እሳቤ ስለሆነ የሌላውን ሰው ባሕርይ፣ ዝንባሌ፣ እሴት ስሜት ላይ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ ነው። በዚህ ምክኒያት ኃይል ተጽዕኖ የማም

---

[77] James Hillman, Kinds of Power (New York:: Currency-Doubleday, 1995), 97.
[78] David C. McClelland and David H. Burnham, "power is the Great Motivator," Harvard Business Review, January - February 1995, 134.
[79] John B. Miner, *Organiational Behavior*, (New York: Random House, 1988), 481.

ጣት አንዱ ክፍል ሊሆን ይችላል::"[80] ስቲፍን ፒ. ሮቢንስ የሚባለውም "ኃይል የሚያመለክተው 'ሀ' በ 'ለ' ላይ ተፅዕኖ ሲኖረውና፣ 'ለ' ደግሞ አንድ ሊያደርገው የማይፈልገውን ነገር ተገድዶ ሲያደርግ ነው::..."[81] ስለዚህ ኃይል ማለት 'ሀ' ያለ የሌለውን ጉልበቱን ተጠቅሞ በ 'ለ' ላይ ተፅዕኖ ሲያመጣና፣ 'ለ' ደግሞ ካለው የተመ ጠነ/ አነስተኛ አቅም የተነሣ በ 'ሀ' የመጣበትን ትዕዛዝ ባይፈልገው፣ ለማድረግ ሲገደ ድ ነው:: 'ሀ' የሚጠቀምበት ኃይል ግን ባለው የውስጥ መነሻ፣ ውስጣዊ ፍላጎት፣ ወይንም ኃይሉን ለመጠቀም አቅም ሊሰጡት የሚችሉ ምንጮች ስላሉት የሚነሣሣ ሊሆን ይችላል::[82]

መሪዎች ምንም እንኳን በሰዎች ( ወይም በሕዝብ ላይ) ተጽዕኖ ለማምጣት የሚ ችሉበት አቅሙ ቢኖራቸውም፣ "መጠቀሚያ መሣሪያዎችን ምንጮችን፣ ገንዘብንና አቅምን" ብቻቸውን ለመቆጣጠር በሚጀምሩበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ማሳየ ት አመራር ሳይሆን፣ ኃይል መጠቀም ነው:: ኃይልን አለ አግባብ የሚጠቀሙ መሪ ዎች ሰዎችን ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቅ መልኩ ከሚቀርቧቸው ይልቅ፣ ሰው መሆናቸውን በሚያስረሳና በሚረግጥ መልክ መመልከት ይጀምራሉ:: ኃይልን ከሚገ ባ በላይ ለጥጠው የራሳቸው መጠቂሚያ የሚያደርጉ መሪዎች ከሕዝቡ እየራቁ፣ ሕዝቡንም፣ እየናቁና አልፎም ተከታይ ብቻ እንደሆነ ያስባሉ::

## ለ. የሥልጣን ትርጉመ ወሰን:-

"ሥልጣን" የሚለው ቃል የመጣው "አክቶሪታስ" ከሚል የላቲን ቋንቋ ነው:: ምንም እንኳን ሥልጣንና ኃይል በአንድነት የሚሄዱ ሐሳቦች ቢሆኑም፣ ሥልጣን ግን ከኃይል ይለያል:: ኃይል "አንድን ሰው በራሱ ቢሆን ሊያደርገው የማይፈልገው ን ነገር አስገድዶ እንዲያደርግ ማድረግ" ሲሆን፣ "ሥልጣን ግን ያንን ኃይል ለመጠ ቀም የሚያስችል ሕጋዊ መንገድ (LEGITMACY) እና ኃይልን ለመጠቀም ሙሉ ድጋፍ (JUSTIFICATION) የሚሰጠው መሪው ካለው የሥልጣን እርከን ጋር የተያ

---

[80] Ibid.

[81] Stephens B. Robbins, *Essentials of Organizational Behvior, 4th. ed.,* (Englewood Cliffs, NJ: Pretice Hall, 1994), 152.

[82] See Burns, *Leadership, 9-28;* Max Weber, *The Theory of Social and Economic Organization,* Talcott Parsons, ed., (New York: Oxford University Press, 1947).

ያዘ ነው::"[83] የሥልጣን ነገር ከተነሣ የተለያዩ ዓነቶች እንዳሉ ማወቃችን አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ:- የወላጆች ሥልጣን÷ የትንንሽ ቡድን ሥልጣን÷ የድርጅቶች ሥል ጣን (ለምሳሌ:- ት/ቤት÷ ካምፓኒ÷ ወዘተ)÷ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን÷ ድርጅታ ዊ መዋቅር ያለበት ሥልጣን÷ እና የአገር አስተዳደር ሥልጣን:: ከእነዚህ ሁሉ የሚ ለው የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ነው:: ሌሎቹ ሁሉ ሰብዓዊ ምንጭ ሲኖራቸው፣ በቤ ተ ክርስቲያን ያለው የሥልጣን ምንጭ ግን እግዚአብሔር ስለሆነ፣ መንፈሳዊ ሥል ጣን ነው:: ይህም ማለት መሪው ለመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን እስከተገዛ ድረስና ለእግ ዚአብሔር ክብርና ለሕዝቡም ጥቅም ለማዋል እስከተጠቀመበት ብቻ ነው መንፈሳዊ ሥልጣን የሚሆነው!!!

ማክስ ዌበር የሚባለው ምሁር በቀድሞ ዘመን በጻፈው መጽሐፍ "ሥልጣን" በተ መለከተ ሦስት ዕይነቶች እንዳሉ አመልክቷል:- "ካሪዝማቲክ፣ ሕጋዊ፣ እና ባህላዊ" ("RATIONAL, LEGAL, AND TRADITIONAL)[84] እንደ ዌበር አባባልና በታርኮ ችም መካከል እንደተገለጸው በመጀመሪያ አንድ መሪ የተከሰተውን ችግር ለመፍታ ት በንግግር የማሳመን ችሎታውና ተስፋ በሚሰጥ የመሪነት ካሪዝማ ይነሣል:: ከዚያ ም በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትንና ዝናን ባገኙ ቁጥር በመጨረሻ የእርሱ አመራር እንደ ባሕል ይወሰዳል::

በቤተ ክርስቲያን ያለው መንፈሳዊ ሥልጣን ግን ከዚህ በጣም ይለያል:: አንድ ም እግዚአብሔር ምንም እንኳን የሰውዬውን የተፈጥሮ ችሎታ ሊጠቀም ቢችልም፣ የሥልጣኑ መሠረት ግን የመሪው የንግግር ችሎታ አይደለም:: በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች ብዙ የመናገር ችሎታ የነበራቸው ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ በአመራር እርከን ላይ ወጥተው ከታዩ በኋላ ደብዛቸው የሌለ "መሪዎች" ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን የሥልጣናችን ምንጭ እግዚአብሔር ነው:: መሪዎችን ለአገልግሎት የሚጠራው፣ የሚያስነሣውና የሚቀባው እግዚአብሔ ር ነው:: መንፈስ ቅዱስ መሪውን በመንፈሱ ከሞላውና ኃይልን ካለበሰው በኋላ፣ በእርሱ አልፎ የሕዝቡን ሕይወት ይዳስሳል:: መልዕክትና መልዕክተኛ የሆነው ጌታ ራሱን በመሪው አገልግሎት ውስጥ ይገልጣል:: በሚደረገው አመራርና አገልግሎት ም ሁሉ በቀኑ መጨረሻ ክብሩ የእግዚአብሔር ይሆናል:: እግዚአብሔር በመሪው ሕይወትና አገልግሎትም ምክኒያት አዲስ የመሪዎች ትውልድንም ያስነሳል::

---

83 Hersey, Blanchard, and Johnson, *Management of Organizational Behavior*,230-231.
84 Weber, *The Theory of Social and Economic Organization*, 1947.

ክርስቲያን መሪ መንፈሳዊ ሥልጣኑን የሚለማመደው በፍቅር እንጂ በኃይል አይደለም፤ በሕይወት ምሳሌነት እንጂ፤ በግዴታ አይደለም፤ በማሳመን እንጂ፤ በመ ጨፍለቅ አይደለም:: መሪዎች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ኃይልና ሥልጣን አላቸው:: ሥልጣን ግን በትክክል እንደ እግዚአብሔር ቃል በሥራ ይተርጎም ከተባለ በትሁታ ን እጅ ሲከናወን ብቻ ነው የጌታን ክብር ማግለጫና የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመታ ነፅ ምክኒያት የሚሆነው:: የትኛውም መሪ ያልተመጠነ ኃይልና ሥልጣን ሊሰጠው ያን ያህል ጥበበኛ አይደለም:: ሎርድ አክተን የተባሉ የታሪክ ፀሐፊ እንዳሉት:- "ኃይል ሰውን እንዲባልግ ያደርጋል፤ መጠን የሌለው ኃይል ደግሞ መጠን በሌለው ሁኔታ እንዲባልግ ያደርገዋል::" ("POWER TENDS TO CORRUPT, AND ABSOLUTE POWER CORRUPTS ABSOLUTELY!!!")[85] የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት አብርሃም ሊንከንም እንዲህ ብለዋል:-"ሁሉም ሰው ተቃውሞን ለመቋቋም ይችላል፤ ነገር ግን የአንድን ሰው ባሕርይ ለማወቅ ካስፈለገ ኃይል ስጠው::"[86] ሥልጣን በገንዘብ የሚገዛ፤ የምንወለድበት፤ ወይም ከላያችን ባሉ መሪዎች የሚሰጥ ሳይሆን፤ ከጠራን ከእግዚአብሔርና በምናገለግላቸው ሰዎች ለእንዲህ ዓይነት አክብሮት የሚገባ የመሪነት ባህርይ ከእኛ ከመሪዎች ካዩ በኋላ የምናገኘው ነው::

- የመጀመሪያው ዓይነት ኃይል የአገልጋይ መሪነት ካላቸው ሰዎች የማሳመ እና ምሳሌአዊ ሕይወት የተነሣ የሚደረግ ነው:: ሁለተኛው ዓይነት ኃይል ግን በማስ ገደድና በመጨፍለቅ (COERCIVEPOWER) ሕዝብን ለመጫንና ለመግዛት የሚደረግ ነው:: በሁለቱ መሀል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ የመጀመሪያው ግለሰ ብም ሆነ ሕዝቡ ያለ ምንም ምርጫ እንዲጎዝ ማድረግ ነው:: ሁለተኛው ዓይነ ት የኃይል አጠቃቀም ሕዝቡ ያለውን እምቅ የጸጋ ስጦታ እንዳይወጣና እንዳ ያድግ የሚያደርግ ከመሆኑም ሌላ፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተመልካች የሚያደ ርግ አሠራር ነው:: በጣም የሚገርመው ግን እንዲህ ዓይነት የኃይል አጠቃቀም ሕዝቡ በበለጠ ሁኔታ መሪውን እንዲጋፉት ያደርጋቸዋል፤ ቢያንስ ያስገድዳቸዋ ል::

---

[85] Lord Acton (April 3, 1887) - English Historian, www.notable-quotes.com/p/power-quotes.html. (accessed August 10, 2013).
[86] Abraham Lincoln (1809-1865), www.goodreaders.com/quotes/tag/power.html. (accessed August 10, 2013).

❖ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚጠይቃቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ። በአመራር ላይ የተቀመጠ መሪ ሁሉ በጥሞና ሊያስብባቸውና ሊመልሳቸው የሚገቡ ጥያቄዎች ናቸው ብዬ አምናለሁ።

❖ **ልታመንበት እችላለሁ ወይ?**
**(TRUST)**
❖ **እኔን ለመምራትና ለመርዳት ይችላል?**
**(RATIONAL INTELLIGENCE)**
❖ **ስለ እኔ ችግር ወይም ጉዳይ ይገደዋል ወይ?**
**(EMOTIONAL INTELLIGENCE)**

## III. የሥልጣንና የኃይል አጠቃቀም:-

### ሀ. ያለ አግባብ ለመጠቀም ምክኒያቶች:-

1. ጌታ ኢየሱስ እንዳለው "የምድር ጨው" እና "የዓለም ብርሃን" ከመሆን ይልቅ (ማቴ. 5:13-16)፣ በዓለም ላይ የሚታይና የበቃ አገልጋይ የመሆን ውጥረት ውስጥ ስንገባ፥ ከእግዚአብሔር በአደራነትና ለዓላማ የተሰጠንን ሥልጣንና ኃይል አለ አግባብ መጠቀም እንጀምራለን። ዓለም ከራሱ የመነጨ ማጣፈጫም ሆነ፣ እንዳይበስብስም ማቆያ ወይም መጠበቂያ የለውም። እግዚአብሔር "የምድር ጨው አድርጉ ያስቀመጠን ክርስቲያኖችን፣ ይልቁንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ነው። እንደዚሁም እኛ "የዓለም ብርሃን" ነን።

ጨው የማጣፈጥ ሥራውንና የማቆየትና እንዳይበሰብስ የመጠበቅ ሥራው የሚሠራው ሲሟሟና እሱነቱ ሳይታይ ለሌላው ጥቅም ባለው አገልግሎት ሲያገለግል ብቻ ነው። ይህንን እየታየ የማይታይ አገልግሎቱን ትቶ ግን ራሱ የሚታይበት መንገድ ከመፈለጉ የተነሣ "እስከ መቼ ሌላውን ሳጣፍጥ እኖራለሁ፣ እኔው ራሴ ወጥ ካልሆንኩ፣" ብሎ ቢታገል የማይረባና የማይጠቅም ይሆንና ወደ ውጭ ይጣላ ል። እንዲሁም ብርሃን የማብራት፣ የማሳየት፣ የማጉላትና፥ የመግለጥ ሥራው የሚያከና

ውነው የሰው ሁሉ ዓይን በእርሱ ላይ እንዳያርግ ጥንቃቄ በማድረግና፣ ከዚህ ይልቅ
የሌላውን ውበት ወይም በሌላው ውስጥ ያለውን ጨለማ በመግለጥ ነው:: ብርሃን
ግን "እኔ እስከ መቼ ነው ራሴን ሰውሬ የምኖረው/ እኔው ብቻ ካልታይሁ!" ቢልና
የሰው ሁሉ ዓይን ወደ ራሱ ቢስብ ሰው ሁሉ ይሸሸዋል::

ጨውም የማጣፈጥ÷ የመመዝመዝና÷ የመጠዝጠዝ÷ ሥርውን አቁሞ አልጫ
ከሆነ (ውሃ÷ ውሃ ካለ)፣ ብርሃንም በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ ሆኖ በጨለማው
ላይ ማብራት ካልቻለ ምንም ረብ የለውም:: ጨው ምንም እንኳን በጣም የረጋ ኬሚ
ካል ኮምፓውንድ መሆኑና ምንም ዓይነት ነገር ለመቋቋም የሚችል መሆኑ ቢታወቅ
ም፣ አንዴ በውስጡ ንፁህ ያልሆነ ነገር ገብቶ ቢበከል ግን ለሌላ ጥቅም የማይውል
ብቻ ሳይሆን÷ እጅግ በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል!!! ዓለም ያለ ጨው እንደተበላሸ
አሣ ይግማማል፣ ይሸታልም:: ብርሃንም እንደዚሁ ሊያበራለት ከተገባው ዓለም ጋር
ከተመሳሰለና በውስጡ የጨለማ ባህርይ ከገባ፣ ዓለምን ወደባሰ ጨለማ አዝቅት ውስ
ጥ እንድትገባ ምክኒያት ይሆናል:: ጨው በባሕርዩ የመጠበቅ ተፅዕኖ በማምጣት
ምድሪቱ እንዳትበሰብስ ይጥብቃል:: ብርሃን ደግሞ አዎንታው ተፅዕኖ በማምጣት
ዓለም በውስጧ ያለውን ጨለማ በብርሃን እንድታይና እንድታስተውል ያደርጋል!!!

2. በእግዚአብሔር በመጠራታችን መካከልና ጥሪ በሚያስከፍለው ዋጋ መካከል
ያለው ግንኙነት ከመጀመሪያው ሳናስተውል ቀርተን፣ ሁኔታዎች እየከበዱ፣ በጥሪያ
ችን ባሕርይ ምክኒያት የሚወዱን ሰዎች ያሉትን ያህል የሚጠሉን እየበዙ ሲሄዱ፣
መከራና ስደት ሲያጋጥመን፣ ከጌታ የተሰጠንን ሥልጣንና ኃይል ወይም ልክ ባልሆነ
መንገድ የተጠራንለትን ሕዝብ በመጫን፣ ወይንም ደግሞ በማመቻመች መምራት
እንጀምራለን:: ለአገልግሎት በጠራን ጌታ ላይ ከመታመንና ከመደገፍ ይልቅ ባለን
ኃይልና ሥልጣን የመታመን ጭንቅንቆሽ ውስጥ እንገባለን::

3. እግዚአብሔር በቅድሚያ እንድናገለግለው የሰጠንን ቤተሰብ (ሚስትና ልጆ
ች) ትተን፣ ትልቁን ቤተሰብ (ማለትም:- ቤተ ክርስቲያን = የክርስቶስ አካል የሆነ
ውን ምዕመን) ለማገልገል የበለጠ ትኩረት ስንሰጥ፣ የግል ቤተሰባችንን እየበተንን፣
ሌሎችን ቤተሰቦችና ግለሰቦችን በማገልገል ጭንቅንቆሽ ውስጥ ስንገባ ከጌታ የተሰጠ
ንን ሥልጣንና ኃይል አለ አግባብ መጠቀም እንጀምራለን::

4. የእግዚአብሔርን ፍቅር ከመፈለግ ይልቅ፣ የኃይል ፍቅር፣ እግዚአብሔርን
ከማምለክ ይልቅ፣ ራስን ለማምለክ በመቋመጥ ጭንቅንቆሽ ውስጥ ስንገባ፣ ከጌታ
የተሰጠንን ኃይልና ሥልጣን አለ አግባብ መጠቀም እንጀምራለን::

5. ሌሎች አገልጋዮችም ሆነ ወንድሞችና እህቶችን ከመውደድ ይልቅ፣ ሁሉን ነገር በእኛ ዙሪያ እንዲሽከረከር ከመፈለግ የተነሣ የውድድርና የፉክክር መንፈስ በውስጣችን ገብቶ ሊነዳንና ጭንቅንቆሽ ውስጥ ስንገባ ከጌታ የተሰጠን ኃይልና ሥልጣን አለ አግባብ መጠቀም እንጀመራለን።

6. ለእግዚአብሔርም ሆነ ለተጠራንለት ሕዝብ ታማኝ ሆኖ ከመገኘት ይልቅ፣ ስኬታማ አገልጋይ ለመሆን ስንታገልና ጭንቅንቆሽ ውስጥ ስንገባ ከጌታ የተሰጠን ሥልጣንና ኃይል አለ አግባብ መጠቀም እንጀምራለን። የመጨረሻ ግብ አድርገን የተነሣንበትን እንጂ፣ ወደ ግቡ የሚወስደውን ሂደት ምንም የማይገደን እንሆናለን።

7. እግዚአብሔር የሰጠን ገንዘብም ሆነ ንብረት በአደራነት እንደተሰጠን አውቀን ዕድሉ ለሌላቸውና ለተቸገሩ ሰዎች፣ ወይም የጌታ ሥራ ለመሥራት እየፈለጉ በገንዘብ ምክኒያት የተጣበቡ አገልጋዮችን ከመደገፍ ይልቅ፣ ሀብታም ወይም ከተቻለ ደግሞ ባለጠጋ ለመሆን በሀልማችንም በውናችንም ይህንን ብቻ የማሰብ ጭንቅንቆሽ ውስጥ ስንገባ ስስታም (GREEDY) እንሆንና ከጌታ የተሰጠንን ሥልጣንና ኃይል አለ አግባብ መጠቀሚያ እናደርገዋለን።

## ለ. የኃይል አጠቃቀም ልዩነቶች:-

የኃይል አጠቃቀም በተመለከተ በሥራ ሲተረጎም የተለያዩ ገፅታዎች እንዳሉና ኃይሉን የሚጠቀምበት መሪውም ሆነ በተግባር ሲገልፀው የሚያየው ሕዝብም እነዚህን ማወቁ ይገባል ብዬ አስባለሁ። የኃይል አጠቃቀሞች በአምስት ዓይነት ገጽታ ልናያቸው እንችላለን:-

- መጠቀሚያ የሚያደርግ ኃይል (EXPLOITIVE POWER)
- የመጫንና የመግዛት ኃይል (MANIPULATIVE POWER)
- የፉክክር ኃይል (COMPETITIVE POWER)
- ድጋፍ የሚሰጥ ኃይል (NUTRIENT POWER) እና
- ወጥነት ያለው ኃይል (INTEGRATIVE POWER)

ናቸው። እያንዳንዳቸውን በመጠኑም ቢሆን ለመዘርዘር እሞክራለሁ።

1. መጠቀሚያ የሚያደርግ ኃይል:-

እንዲህ ዓይነት የኃይል አጠቃቀም ሰዎች አመኑበትም አላመኑበትም በግዴታ ኃይሉን ለመጠቀም ስለሚፈልግ በባህርዩ አፍራሽና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያመጣ ነው::

2. የመግዛት ኃይል:-

ይህ ዓይነት የኃይል አጠቃቀም መሪ በግለሰብ ወይም በሕዝብ ላይ ለመሰልጠን ሲፈልግ ኃይሉን በመጫን ይጠቀማል:: ከዚህ የተነሣ አቅም የሌላቸውን ሰዎች ያለአግባብ ሊገዛቸው ይችላል::

3. የፉክክር ኃይል:-

እንዲህ ዓይነት የኃይል አጠቃቀም መሪው ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ካለው የውደደርና የፉክክር መንፈስ የተነሣ ኃይሉን ያለ አግባብ ስለሚጠቀም አብዛኛውን ጊዜ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣል::

4. ድጋፍ የሚሰጥ ኃይል:-

ይህ ዓይነት የኃይል አጠቃቀም የምናገኘው ለምሳሌ ወላጆች ልጆቻቸውን ለመርዳት የሚጠቀሙት፣ ወይም ፓስተር የሚያገለግላቸውን ሰዎች ለመደገፍ የሚ ጠቀመው የኃይል አጠቃቀም ነው:: አብዛኛውን ጊዜ አዎንታዊ ተፅዕኖ ስለሚያመ ጣ ተፈላጊነቱ የሚያጠራጥር አይደለም::

5. ወጥነት ያለው ኃይል:-

እንዲህ ዓይነት የኃይል አጠቃቀም መሪው ያለውን ኃይል ከሚያገለግለው ሕዝ ብ ጋር፣ ወይንም ከሌሎች አገልጋዮችና መሪዎች ጋር በማስተባበር የበለጠና የከበረ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ሲጠቀምና የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያሳፋ ነው::

## ሐ. የኃይል አጠቃቀማና የመለወጥ ዕድገቶች:-

የኃይል አጠቃቀም በሚመለከት ጉዳይ ቀደም ብለን እንዳየነው ልዩ ልዩ ገፅታ ዎች ያሉትን ያህል፣ አሁን ደግሞ አመለካከታችንን በመለወጥ ሕዝብን ለማገልገል የመለወጥ ዕድገቶች እንዳሉ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ:: እግዚአብሔር የሰጠን ኃይል በጥበብ፣ በማስተዋልና የተጠራንለትን ሕዝብ ለማሳደግ ከተጠቀምንበ ት የእግዚአብሔርን ሕዝብ፣ ያለን ራዕይና በዓላማ የተነሣንባቸውን አገልግሎቶች

ጌታን በሚያስከብር መልኩ ፍፃሜ ላይ ማድረስ ያስችለናል። በውስጣችን ያለው የማሰብ፤ የማጤንና የማስተዋል ኃይል በውጭ ከሚገልፀው (በሥራ የሚተረጎመው) ኃይል ጋር ማጣጣም (ማስማማት) መቻል ብዙ የከበሩ ውጤቶችን ሊያመጣ ይችላል። የመለወጥ ዕድገቶችን በተመለከተ ጄነትአ ሃግበርግ የምትባል ሰው ስድስት የመለወጥ ዕድገቶች እንዳሉ የገለፀቻቸውን ሐሳቦች እንደሚከተለው አቀርባለሁ።[87]

1. "ኃይል የለሽ":- ("POWERLESSNESS")

በዚህ ደረጃ መሪዎች እርግጠኝነት ያላቸው እና መደገፍ የሚወዱ፤ ምናልባትም አቅም የሌላቸው፤ ነገር ግን ተስፋ በማጣት ልባቸው ያልወደቀ አድርገን ልንገልፃቸው እንችላለን። ፍርሃት በውስጣቸው ስላለ እውነተኛና ንፁህ የሆነ ኃይል መጠቀም ያልቻሉ ናቸው።

❖ <u>እንዲህ ዓይነት መሪዎች ካላቸው ፍርሃት የተነሳ አመራራቸውን የሚገልፁት በጉልበት እና በማስፈራራት መልክ ነው</u>።

2. "ኃይል በሌላው ላይ በመታከክ":- ("POWER BY ASSOCIATION")

በዚህ ጊዜ መሪዎች ኃይላቸውን የሚጠቀሙት ከላያቸው በተቀመጡ ሌሎች ታዛቢ መሪዎች በማስታከክ ነው። እነዚህ መሪዎች ለመለውጥና ለማደግ በመፈለግ፤ በእግራቸው መቆምና ቢያስፈልግም ዋጋ የሚያስከፍል እንኳ ቢሆን ሳይታገዱ አገልግሎታቸውን መፈጸም፤ የብቃት ለውጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

❖ <u>እንዲህ ዓይነት መሪዎች አመራራቸውን የሚገልጹት በማጭበርበር እና ሌሎች በእነርሱ እንዲደገፉ በማስገደድ ነው</u>።

3. "ኃሉን በማሳየት":- ("POWER BY SYMBOLS")

በዚህ ደረጃ ያሉ መሪዎች አመራራቸውን የሚገልፁት በመቆጣጠር ስለሆነ የኃይል ጥማት የሚጠናወታቸው፤ በጣም ትፎካካሪ፤ ካሪዝማቲክና ራስ ወዳድ በመሆናቸው ይታወቃሉ። እነዚህ መሪዎች ዝርዝር ነገሮችን በመቆጣጠር (MICRO-MANAGEMENT) አመራራቸውን ስለሚገልፁ ወደሚቀጥለው ምዕራፍ እንዳይሸጋገሩ ይይዛቸዋል።

---

87 Janet O. Hagberg, *Real Power: Stages of Personal Power in Organizations*, (Salem, Wis.: Sheffield, 1994), xxi; see also Banks and Ledbetter, *Reviewing Leadership*, 32-33.

❖ ሌሎችንም በማሳመን ስለሚመሩ ሕዝቡ የአሸናፊነት ዝንባሌ እንዲኖረው ያደርጋሉ::

4. "ኃይልን በማገናዘብ"፡- ("POWER BY REFLECTION")

በዚህ ደረጃ ያሉ መሪዎች አመራራቸውን የሚገልፁት ሌሎችን በመማርክና በእነርሱም ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ በማምጣት ስለሆነ፣ ብርቱዎች፣ ማመዛዘን የሚችሉ፣ ብቃት ያላቸውና ሌሎችን በማሳደግ ችሎታ ያላቸው መሪዎች እንደሆኑ ይታወቃል::

❖ በመልካም አመራራቸውና ወጥነት ባለው ሕይወታቸው ስለሚታመኑ ተስፋን የሚያድሱ ናቸው::

5. "ኃይልን በዓላማ"፡- ("POWER BY PURPOSE")

በዚህ ደረጃ ያሉ መሪዎች አመራራቸውን የሚገልፁት ከራሳቸው ያለፈ ትልቅ ራዕይ ስለሆነ የራሳቸው አጀንዳ የላቸውም:: ከዚህ የተነሣ ያላቸውን ኃይል ለሌሎች ማካፈልም ይሁን፣ ወይም ቦታ ለመልቀቅና ሌሎች እንዲመሩ ለማድረግ ልቡ አላቸው:: በሌሎች አመራር ሥር ለመቀመጥም ደስ ይላቸዋል::

❖ እነዚህ መሪዎች ሌሎችን በማጎልበት ስለሚመሩ በሚመሩአቸው ሰዎች ላይ ፍቅር፣ አገልጋይነትና መስጠትን ያነሣሣሉ::

6. "ኃይልን በጥበብ"፡- ("POWER BY GESTALT")

በዚህ በመጨረሻው ደረጃ ላይ ያሉ መሪዎች አመራራቸውን የሚገልፁት ኃይልን በጥበብ በመግለፅ ነው:: እነዚህ መሪዎች "የዓለም ነፍስ" ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ውስብስብ በሆኑ ሁኔታዎች መሀል የተረጋጉ፣ ሞትን የማይፈሩ፣ በጸጥታና በእርጋታ አገልጋይ መሪዎች የሆኑ፣ እና የሞራልና የሥነ-ምግባር መለኪያቸው ከፍተኛ የሆኑ መሪዎች ናቸው::

❖ የእነዚህ መሪዎች አመራር እየታየ የማይታይ (VISIBLE INVISIBLE) ስለሆነ በእነርሱ በሚገለገለው ሕዝብ ልብ ውስጥ እርካታን፣ ጸጥታንና ሰላምን ስለሚፈጥር በእነርሱ የሚገለገለው ሕዝብ የታደለ ነው!!!

## መ. የመጽሐፍ ቅዱስ እይታ:-

እላይ የጠቀስናቸውን ሐሳቦች ማየቱ መልካም ሆኖ እያለ፣ የእግዚአብሔር ቃል ስለ አመራርና የሥልጣንና የኃይል ጥያቄ የሚለውን መዳሰሳን በጣም ወሳኝ ነው:: ምክኒያቱም ስለ ሕይወታችን፥ ስለ አገልግሎታችንና፥ ስለ አመራራችን የመጨረሻው ቃል ያለው ሥልጣን የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ስለዚህ የበለጠ በትኩረት ለማየት እንዲያመቸን ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አመራርና የሥልጣንና የኃይል ጥያቄን በሚመለከት የነበረውን መረዳት ለመዳሰስ እንሞክራለን::

ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን አመራርን በተመለከተ በልዩ ዘዴ ያስቀመጠው ባይኖርም፣ የአመራርን ባሕርይና የሥልጣንና የኃይል አጠቃቀም በሚመለከት ብዙ ሊያነጋግሩን የሚችሉ ጥያቄዎች ከራሱ ሕይወትና ከጻፋቸው መልዕክቶች ለመረዳት እንችላለን::[88]

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በመጀመሪያው መልዕክቱ የቤተ ክርስቲያንን መልክ በጠራ ሁኔታ ለማየት የሚያስቸግር ውስብስብ ነገር ይመስላል:: የቆሮንቶስ ቤተ ክርቲትያን ስለ ራስዋ የነበራት መረዳትና የነበረችበት ሁኔታ መሃል የማይጣጣም ነበር:: እግዚአብሔር ያስቀመጠው መለኪያና የቤተ ክርስቲያኒቱ እውነታ አብሮ የማይሄድ ነበር:: "ለክርስቶስ በታጨች" ቤተ ክርስቲያን መሃልና ፍቅር የለሽ ፤ ቅድስና የጎደለው፣ በየጊዜው የሚጠላላ ሕብረተሰብ በመሆኗ መካከል ብዙ ልዩነት ነበረው:: በመጨረሻው ዘመን በሚጠብቃት ክብርና፥ አሁን ያለችበት ሁኔታ፥ በሰማያዊ መዳረሻዋና፥ አሁን በምድር ያለው ክብር የሌለው ሁኔታዋ መሃል የማይጣጣማና የሚጋጭ ነበር::

### 1. ሐዋርያት እነ ማን ናቸው?

በምዕራፍ 1:1 ላይ ጳውሎስ ስለ ራሱ "በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ ጳውሎስ" የሚለውን ሐሳብ መነሻ በማድረግ "ሐዋርያት እነማን ናቸው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክራለን:: በመሠረቱ "ሐዋርያ" የሚለውን ስያሜ የተጠቀመው ጌታ ኢየሱስ ሲሆን፣ የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለቱ

[88] See Robert Banks, *Paul's Idea of Community: The Earthly House Churches in Their Historical Setting*, (Peabody, MA: Henrickson, 1994).

ን ደቀ መዛሙርትና ከዚያም በኋላ ጳውሎስ፣ ያዕቆብና በርናባስንም (ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል) የሚያጠቃልል ነው።

❖ ሐዋርያት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ በግላቸው የተመረጡ፣ የተጠሩና የተሾሙ ናቸው እንጂ፣ "*ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆኑ*" (ገላትያ 1፡1) ማለትም፣ ሰዎች እንዲሆኑላቸው ስለፈለጉ፣ ወይም ስውዬው ራሱ ሐዋርያ ለመሆን ስለፈለገ አይደለም።

❖ ሐዋርያት በታሪክ መካከል የተገለጠው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የዓይን ምሥክሮች ሆነው የአደባባይ አገልግሎቱንም ለሦስት ዓመት ትኩል የተመለከቱ ናቸው። (ማር. 3፡13-14፣ ዮሐ. 15፡27) ከዚህም በተጨማሪ የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ የገል ምሥክሮች ናቸው። (የሐዋ. ሥራ 1፡21-22፣ 2፡23-24፣ 3፡15 4፡33 ወዘተ) ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን ሐዋርያነት ሲያስረግጥ "እኔ ሐዋርያ አይደለሁምን? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንስ አላየሁትምን? (1ቆሮ. 9፡1) ብሎ ይናገራል።

❖ ሐዋርያት የእውነት መንፈስ የተሰጣቸውና በመንፈስ ቅዱስ በመመራት በዘመናት ተሠውሮ የነበረው የእግዚአብሔርን ምሥጢር መገለጥ (<u>REVELATION</u>) መረዳቱ የተሰጣቸውና ይህንንም መገለጥ በጽሁፍ ለማስፈር የመንፈስ ቅዱስ ምሪት (<u>INSPIRATION</u>) የነበራቸውና ለዚህም የተጠሩ ሰዎች ናቸው። ይህንን የከበረውን የእግዚአብሔር ምሥጢር ክርስቶስ ኢየሱስን ለሰዎች በሚገባ መንገድ በመግለጥ፣ በመስበክና በማስተማር (<u>ILLUMINATION</u>) የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነውን የመሠረቱናቸው። (ቆላ. 1፡25-29፣ ዮሐ. 16፡12-15፣ 1ጴጥ 1፡12፣ 2ጴጥ. 1፡20-21፣ ኤፌ.2፡20)

❖ ሐዋርያት እግዚአብሔር በእጃቸው ተአምራት፣ ምልክትና ድንቅ እንዲከናወን የተጠቀመባቸውና የሚጠቀምባቸው የጌታ ልዩ ቅባት ያላቸው ናቸው። (2ቆሮ. 12፡11-12፣ ሮሜ 15፡18-19፣ የሐዋ ሥራ 3፡6-8፣ 5፡12፣ 14-16፣ 19፡11-12፣ ወዘተ)

❖ ሐዋርያት በግል ሕይወታቸውም ሆነ፣ በአገልግሎታቸው ንጽሕና እና ወጥነት ያላቸው ሰዎች ከመሆናቸው የተነሣ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው የአብያተ ክርስቲያናት መለኪያ ነው። የሚኖሩትን የሚሰብኩ፣ የሚሰብኩትን የሚኖሩ ናቸው።

❖ ሐዋርያት የተሰጣቸው የሐዋርያነት ሥልጣን ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንጂ፣ ለማፍረስ እንዳልሆነ፣ የክርስቶስን አካል ለማጎልበት እንጂ፣ ለማቀጨጭ እንዳል ሆነ ስለሚያስተውሉ የሕይወትም ሆነ የአገልግሎት አቀርቦታቸው ቅንነት ያለ ው (GENUINE)፣ ነባራዊነት ያለው (ORIGINAL)፣ የትህትና መንፈስ ያለው (HUMBLE SPIRIT)፣ ከስኬታማነት ይልቅ፥ ታማኝነት ላይ ያተኰረ ነው:: (ቆላ. 1:25፣ 2ቆሮ 10:8፣ 13:10፣ ፊል. 2:20-21፣ 1ቆሮ. 2:1-5)

2. የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ገጽታ:-

ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን ይህ የአማኞች ሕብረተ ሰብ "የእግዚአብ ሔር ቤተ ክርስቲያን" መሆኑ ባይክድም፣ በመካከላቸው ከነበረው መለያየት የተ ነሣ ሊታመንባቸው ስላልቻለ ግን "በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክር ስቲያን" ብሎ ነው የጻፈላቸው:: (1ቆሮ. 1:2) ስለዚህ የቆሮንቶስ ሰዎች:-

- ❖ <u>ሁለት ዓይነት መኖሪያ</u>- ምድራዊና ሰማያዊ፣ በቆሮንቶስና በክርስቶስ ውስጥ፣
- ❖ <u>ሁለት ዓይነት የሕይወት ደረጃ</u>:- እውነታ እና ሊሆኑት የሚችሉት፣ የተቀደሱ እና ቅዱሳን ለመሆን የተጠሩ"፣ እና
- ❖ <u>ሁለት ዓይነት ጥሪ</u>:- እግዚአብሔር ቅዱሳን እንዲሆኑ የጠራቸውና እነርሱም እንዲቀድሳቸው ወደ እግዚአብሔር መጠራት (መጸለይ) ያለባቸው ናቸው::

የቆሮንቶስ ቤተ ክርስትያን ሌላው ገፅታዋ የሚከተሉትን ሦስት ጣምራ እውነቶች የሚያካትት ነው::

- ❖ በመጀመሪያ የክርስቶስ መምጣትና በክርስቶስ ዳግም መምጣት መካከል፣
- ❖ ክርስቶስ ሊያደርገው በመጣውና ከዚህ በኋላ ሊያደርገው በሚመጣው ዘመን መካከል፣ እና
- ❖ በመጣው የእግዚአብሔር መንግሥትና በሚመጣው የእግዚአብሔር መንግ ሥት መካከል የምትኖር ቤተ ክርስቲያን ነች::

ጆን ኒውተው የሚባል ጸሐፊ እንዲህ የሚል ሐሳብ የገለፀው እላይ ለገለፅናቸው የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ገጽታ ማጠቃለያ ነገር ይሆናል፡- "አሁን የሆንኩት ልሆን ው እንደሚገባኝ አይደለም፤ ልሆነው የምፈልገውም አልሆንኩም፤ በሌላው ዓለም ልሆነው የምችለውም አልሆንኩም። ነገር ግን አሁን ያለሁት ከዚህ በፊት በነበርኩበ ት አይደለም፤ እና በእግዚአብሔር ፀጋ የሆንኩትን ሆኛለሁ።"[89]

3. ሐዋርያው ጳውሎስና የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን፡-

- ሐዋርያው ጳውሎስ ለረዥም ጊዜ የቆየና የጠበቀ፤ ግላዊና የመጋቢነት ግንኙነት ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ነበረው። (2ቆሮ. 10:14፤ 1ቆሮ. 3:6፤ 10፤ 4:14-15)
- ሐዋርያው ጳውሎስ ቢያንስ ሦስት ጊዜ ከመጎብኘቱም ሌላ፤ ቢያንስ አራት ጊዜ ም ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጽፏል። ከአራቱም መልዕክቶች ውስጥ ሁለት ብቻ ነው (ማለትም አንደኛና ሁለተኛ መልዕክት) በእጃችን ያሉት።
  - አንደኛ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሰላምታ ፅፏል (ቁ1-3)
  - ሁለተኛ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያመሰግናል (ቁ. 4-9)፤
  - ሦስተኛ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ልመና ያቀርባል።(ቁ. 10-1 በእነዚህ ክፍሎች ሁሉ ሐዋርያው ጳውሎስ አንድ ዋና የቤተ ክርስቲያኒቱ ባህርይ የሚገልጥ ነገር ላይ ሲያተኩር እናየዋለን። ይኸውም የቆሮንቶስ ቤተ ክርስ ቲያን ቅድስናዋ (ቁ. 1-3)፤ ሥጦታዋ (ቁ. 4-9)፤ እና አንድነቷ (ቁ10-17) በጣም የተወሳሰበ ሁኔታና ግልፅነት የሌለው መሆኑን ነው።

<u>አንደኛ</u>፡- ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን "የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን" ሲገልፃት ስናይ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቅድስና የጎደለው ሕይወት በተቀ ደሰች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳለ ይገልፃል። ምክኒያቱም በመካከላቸው መጠላላ ት፤ ትዕቢት፤ ግድየለሽነት፤ ዝሙት፤ የትዳር ፍቺ መኖሩ ብቻ ሳይሆን "ፍትህ" ፍለ ጋ ወደ ፍርድ ቤት መጓተት፤ በአምልኮ መካከል ሥርዓት የለሽ የአደባባይ / የጉባዔ ልምምድ እና በፀጋ ስጦታቸውም ምክኒያት ትምክተኝነት የሚታይባት ቤተ ክርስቲ ያን ነች። (1ቆሮ. 3:1-4)

---

[89] John Newton, quoted by J. C. Ryle in the chapter *"Are You Regenerate?" in Home Truths*, 9th. ed., (London: Chas. J. Thynne., n.d.), 94-95.

ሁለተኛ:- ሐዋርያው ጳውሎስ በሌላ በኩል ስለ እነርሱም በእግዚአብሔር ፊት የሚያመሰግንባቸው ነገሮች አሉ:- ለእነርሱ ስለተሰጠው የክርስቶስ ኢየሱስ ፀጋ (ቁ. 4-5)፤ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ያለው ታማኝነት (ቁ. 9) "...የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው::" (2ቆሮ. 1:18)

ሦስተኛ:- ሐዋርያው ጳውሎስ የእነርሱ አንድነት፥ በልዩነታቸው እንደሆነ (UNITY IN DIVERSITY) በማሳሰብ (ኤፌ. 4፥ 4-6) ልመና ያቀርብላቸዋል:: ምክኒያቱም አንድ አባት ስላለ፤ አንድ ቤተሰብ አለ፤ አንድ መንፈስ ስላለ፤ አንድ አካል አለ፤ አንድ ጌታ ስላለ፤ አንድ እምነት፤ ተስፋ፤ እና ጥምቀት አለ:: ይሁን እን ጂ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ያላቸውን አንድነት ከመጠበቅ ይልቅ፤ ሲበጣጠሱና ሲለያዩ ማየት የሐዋርያው ጳውሎስን ልብ ያሳዘነ ጉዳይ ነበር::

ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መለያየት ዋናው ምክኒያቱ በመመሪያዎች ልዩነት ሳይሆን፤ በግለሰቦች ዙሪያ ራሳቸውን በማስጠለላቸው የመጣ ችግር ነው:: በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ሕዝብ በቡድን በመለያየትና በመከፋፈል "የሚመለ ክ ግለሰብ" ("PERSONALITY CULT") በማድረጋቸው በትዕቢት፥ በቅንዓት እና በትምክህተኝነት ውስጥ መግባታቸውን የጳውሎስ ልብ በጥልቀት የጐዳ ጉዳይ ነበር:: ምንም እንኳን በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ልዩነትና መከፋፈል ምክ ኒያቱ ዶክትሪን ባይሆንም፤ በአንድምታ ግን ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል የነበራቸው መረዳት ጥልቅ የሆነ የዶክትሪን ችግር እንደነበራቸው ለመገንዘብ አያዳግተንም:: (1ቆሮ. 1:12-13) በዚህ ባህርያቸው ምክኒያት የክርስቶስ ማንነት፤ የክርስቶስ መስቀ ልና የክርስቶስ ስም አደጋ ላይ እንዲሆን አድርጎታል:: የክርስቶስን ጌትነትና ሉዓላዊነት የሚጋፋ ባህርይ መግለፃቸው ሐዋርያው ጳውሎስን አሳስቦታል::

ይህንን ሐሳብ ለማጠቃለል ሁለት ጥግ የሆኑ አመለካከቶችን መጥቀስ አስፈላጊ ነው:: በአንድ በኩል እኛ ክርስቲያኖች "ፍፁምነት ያለንና፥ ፍፁምነት ያላትም ቤተ ክርስቲያን" እንድትኖር የምናልም አይደለንም:: እዚህ ላይ ዶ/ር ቢሊ ግራሃም ያሉትን ሐሳብ መጥቀስ እፈልጋለሁ::

"ምንም ቢሆን ፍጹም የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለማግኘት ፈልግ፤ ስታገኛትም የዚያ ች ቤተ ክርስቲያን አባል ሁን:: ነገር ግን አንተ እስዋው ውስጥ ስትገባ ፍጹምነቷ እንደሚቀር አትርሳ::"

❖ ስለዚህ ፍጹምነትን ለሚጠብቁ ሰዎች እንዲህ እንላቸዋለን:- "የቤተ ክርስቲያን ን ንጽሕናን መጠባበቃችሁ መልካም አድርጋችኋል:: የዶክትሪንም ሆነ የሥነ ምግባር ንጽሕና መጠባበቅ ግሩም የሆነ ግብ ነው:: ነገር ግን መደረስ አለበት በ ማለታችሁ ግን ተሳስታችኋል::"

❖ በሌላ በኩል በግድየለሽነት ለሚመሳለሱትና ከቤተ ክርስቲያን ምንም ነገር ለማ ግኘት አንችልም ላሉት ደግሞ እንዲህ እንላቸዋለን:- "በቤተ ክርስትያን ውስጥ ያለውንኃጢአትና ስህተት ዓይናችሁን ሳትዘጉ፣ እውነታውን መቀበላችሁ መል ካም ነው:: ነገር ግን ለኃጢአትና ለስህተት አሠራር ግድየለሽ ሆናችሁ እጃችሁ ን አጣምራችሁ መመሳለሳችሁ ልክ አይደላችሁም:: በቤተ ክርስትያን ውስጥ ኀጢአት ያደረጉ ሰዎችዲሲፕልን መደረግና ካስፈለገም ከቤተ ክርስቲያን አባል ነትም መሰረዝ አለባቸው::" የክርስቶስን መለኮታዊነትና ሰብዓዊነት መካድ የክ ርስቶስ ተቃዋሚ መሆን ነው:: (1ዮሐ. 2:22) የጸጋን ወንጌል መካድም በእግዚአ ብሔር ፊት ፍርድ የሚያስመጣ (ANATHEMA) ነው:: (ገላትያ 1:6-9) የቤተ ክርስቲያንን ገፅታ ሙሉ የሆነ መረዳት እንዲኖረን ካስፈለገ ሐዋርያው ዮሐንስ "ወዳጆች ሆይ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አል ተገለጠም::" (1ዮሐ. 3:2) እንዳለው፣ "አሁን ግን ገና" ("THE ALREADY AND NOT YET! የሚለውን የሥነ መለኮት ሐሳብ በእነዚህ እውነቶች መሃል ያለውን ውጥረት በጥበብና በማስተዋል፣ በትዕግሥትም ልንይዘው የሚገባ እውነ ት ነው!!!

4. ኃይል በድካም ውስጥ ሲገለጥ (1ቆሮ. 1:18-2:5)

❖ "የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም::" (1ቆሮ. 1:17)

❖ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና::" (1ቆሮ. 1:18)

❖ "ለተጠሩት ግን... የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው::" (1ቆሮ. 1:24)

❖ "...ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር እንጂ፣ በሚያባብ ል በጥበብ ቃል አልነበረም::" (1ቆሮ. 2:4)

❖ "እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፤..." (1ቆሮ. 2:3)

❖ "ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን::" (2ቆሮ. 4:7)

❖ ጌታ እግዚአብሔር ለጳውሎስ "*ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌም በድካም ይፈጸማልና አለኝ*" ብሎታል:: (2ቆሮ. 12:9)

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ኃይልን በተመለከተ ስምንት ጊዜ ተገልፆ እናያለን:- የእግዚአብሔር ኃይል፤ የክርስቶስ ኃይል፤ የመስቀሉ ኃይል፤ እና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል:: "ኃይልን" በሚያመልክ ሕብረተ ሰብ ውስጥ ስንኖር እንደ ክርስቲያን መሪዎች ልናስተውለው የሚገባን ነገር ሁሉ የሚያጠነጥነው በእኛ ዙሪያ ሳይሆን በእግዚአብሔር አብ፤ በእግዚአብሔር ወልድና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ላይ ነው:: ክርስቶስና መስቀሉ ሁልጊዜ በፊታችን ልናኖረው ይገባል!!! ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል:- "በመካከላችሁ ሳልሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና::" (1ቆሮ. 2:2) ኃይልን ለማግኘት የመጓጓት፤ የማምለክና፤ የማመንዘር ጉዳይ ከአዳምና ሔዋን፤ የራሳቸው እግዚአብሔር ለመሆን በሰይጣን ከተፈተኑበት ጊዜ ጀምሮ በታሪክ ውስጥ የታየ ባህርይ ነው::

በአሁኑ ዘመንም ሰው ኃይልን ለማግኘት ከመፈለግ ጋር በተገናኙ በሦስት ክፉ ምኞቶች ሲጠላለፍ እናየዋለን:- ገንዘብ፤ ዝና እና ሌላውን መግዛት:: በጣም የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን እነዚህ የሚያጥመነምኑ ክፉ የምኞት አዘቅቶች በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ መከሰታቸውን ስናይ፤ የሚያስስብ ደረጃ ላይ እንዳለን ለመገንዘብ አያዳግተንም:: ከእነዚህም መካከል በቤተ ክርስቲያን የማያፈናፍን መዋቅር በመኖሩ ምክኒያት በመሪዎች መካከል ብዙ መገፋፋትና መጠላላት መኖሩ በቤተ እምነቶች መካሰስ መኖሩ፤ በሽምግልና የተቀመጡ መሪዎች ጌታ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት በጠራቸው ፓስተሮችና አገልጋዮች ላይ እጃቸውን እያከበዱ መምጣታቸውና፤ የአገልጋዮቹ የጸጋ ስጦታና እምቅ ችሎታ እየተፈለቀቀ እንዲወጣ ጸጋን ከመጨመር ይልቅ፥ ራዕያቸውን እያጨናገፈ መምጣቱን፤ በምናይበት ጊዜ ችግሩ የጠለቀ እንደሆነ ለመገንዘብ አያቅተንም::

ከዚህም ሌላ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኃይልን ለማግኘት ያለን "ግላዊ የሥጋ ፍላጎት" "የመንፈስ ቅዱስን ኃይል" ለማግኘት ካለን ጥማት ጋር ተደ

ባልቆ መከሰቱ እጅግ የሚያሳስብ ነገር ነው!!! እንደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ፣ እንደ መሪዎችና አገልጋዮች የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በንጽሕና፣ በቅንነትና የእግዚአብሔ ርን መንግሥት ለማስፋት ከመፈለግ የተነሳ ያልተጠማን ምን እንጠማለን? ነገር ግን ይኸው ጥማታችን ዘወርዋራ በሆነ አዕምሮ፣ "በኃይል ለመሰልጠን" ካለን የግል አጀ ንዳና "በሕዝብ የታወቀ ዝነኛ አገልጋይ" ለመሆን ካለን ውስጣዊ ረሃብ ጋር ሲደባለ ቅ ግን ንጽሕናውን ያጣል!!! እንዲህ ላለው ግላዊ ዓላማ እግዚአብሔር የመንፈሱን ኃይል ለመስጠት እጅግ ይቸገራል:: "ኃይልን ለማግኘት ለምን እንፈልጋለን?" የሚ ለውን በማስተዋል ቆም ብለን ልናስበው ይገባል ብዬ አምናለሁ:: የክርስቶስ ምስክር ለመሆን (የሐዋ. ሥራ 1:8)፣ ለመቀደስ እና ትሕትና የተሞላበት አገልግሎት ለመስ ጠት፣ ወይንስ የግል አጀንዳ መሸፈኛ፣ የውስጣችን ግላዊ ክብር ለማጎልበት አስፈላጊ ወይንም ተፈላጊ አገልጋይ ለመሆን፣ በሌሎች ሰዎች አዕምሮ ለመታሰብ፣ ሌሎችን ለመጫን ከመፈለግ? (ማር. 10:42-44፣ 1ጴጥ. 5:2-3)

❖ አንደኛ ኃይል በድካም ውስጥ ሲገለጥ የምናየው ወንጌል በሆነው በክርስቶስ ነው፣ ምክኒያቱም በመስቀሉ የታየው ድካም ነው የእግዚአብሔር ኃይል ሆኖ የተገለፀው:: (1ቆሮ. 1:17-25)
❖ ሁለተኛ ኃይል በድካም ሲገለጥ የምናየው በቆሮንቶስ ከተማ ባሉት አማኞች ውስጥ ነው፣ ምክኒያቱም "...ብርቱንም ነገር እንዲያሣፍር፣ እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፣..." (1ቆሮ. 2:1-5)

ይህንን ሐሳብ በመቀጠል ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለት ዓይነት ሕዝቦች እንዳሉ ከገለፀ በኋላ፣ የክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን እይታ ከእነርሱ አመለካከት እንደ ሚለይ ይገልፃል:: አንደኛው ሕብረተ ሰብ የአይሁድ ሕብረተ ሰብ ሲሆን፣ "መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣" (1 ቆሮ. 1:22) ይላቸዋል:: መሲህ ለመሆኑ ማረጋገ ጫ ፍለጋ ምልክትን እንዲያሳያቸው ሲጠይቁ እናያለን:: ለዚህ ነው "መምህር ሆይ፣ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን::" ይሉት የነበረው:: (ማቴ. 12:38፣ 16:1፣ ማር. 8:11፣ ሉቃስ 11:16፣ ዮሐ 2:18፣ 4:48፣ 6:30):: ሁለተኛዎቹ ሕብረተ ሰብ የግሪክ ሰዎች ናቸው፣ "የግሪክ ሰዎች ጥበብን ይሻሉ፣" ይላቸዋል:: (1ቆሮ. 1:22) ግሪኮች ለረዥም ዘመን በጣም የሚያስደንቅ ፍልስፍና የሚያፈልቁ ስለ ነበሩ፣ ሰው የሚያስብ አዕምሮ ያለው እንዲሆን የአዕምሮ ነፃነት ፈላጊዎች ነበሩ:: በአሁን ዘመን

ም ቢሆን የኃይል ጥያቄና ሥጋዊ ጥበብን የማግኘት ጥማት የብዙ ክፍለ ዓላማት ውድቀትን የሚገልፅ መሠረታዊ ጣዖታት ናቸው።

ከእነዚህ ሁለት የተለያዩ አጉል የሆኑ አስተሳሰቦች፣ ማለትም "የአይሁድ ኃይል ፈላጊነት" እና "የግሪኮች ጥበብ ፈላጊነት" የተለየ፣ ሦስተኛው እይታ የክርስቲያን አማኞች ርትዕ ያለው አቋም ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክር ስቶስን እንሰብካለን።"* (1ቆሮ. 1፡23) ያለው ነው። የክርስቲያን ስብከት ወይ እንደ አይሁድ አይጠይቅም፥ ኃይልንም ለማግኘት አይቋምጥም፣ ወይንም ደግሞ እንደ ግሪኮችም ሥጋዊ ጥበብ ፍለጋ፥ በሌላው ሰው ላይ ለመሰልጠን ሰብዓዊ ፍልስፍና ለማግኘት አይኳትንም። ነገር ግን *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን።"* እንደ ተባለ ነው!!!

የተሰቀለው ክርስቶስ ለአይሁድ ማሰናከያ፣ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነበር። የመ ስቀሉ ምስጢር ኃይል ለሚያመልኩ ለአይሁድ ሕብረተ ሰብ ፍጹም ማሰናከያ ነበር፣ በፍልስፍና ለናዘለ ለግሪክ ሕብረተ ሰብ ደግሞ ውርደት ነው። የሮም ነዋሪ የሆነና ነፃ የሆነ ሰው በመስቀል አይሰቀልም። " *ለተጠሩት ግን... የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።"* (1ቆሮ. 1፡24)

**5. መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ቃል፡- (1ቆሮ. 2፡ 1-16)**

ሐዋርያው ጳውሎስ የላቀና የተለየ ሌላ "ጥበብ" እንዳለ ለመግለፅ፡- "*በበሰሉት መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን፣ ነገር ግን የዚችን ዓለም ጥበብ አይደለም።"* ይላል። (ቁጥር 6)

- <u>አንደኛ</u>፡- "በበሰሉት መካከል የሚነገር ጥበብ" ነው። የመስቀሉ ምስጢር ገብቷቸው እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው ዓላማ በክርስቶስ መስቀል በኩል በሙላት ሊገቡ የሚ ችሉት የበሰሉ የነጠሩና የባህርይ ለውጥ ሂደት ውስጥ የገቡ ክርስትያኖች ናቸው።
- <u>ሁለተኛ</u>፡- ይህ ጥበብ ከእግዚአብሔር የመጣ ነው። (ቁ. 7) የዚች ዓለም ጥበብ፣ ወይንም በዘመኑ ከሚናፈሰው ኃይልንና ሥልጣንን ለማግኘት ከመጓጓትና ከመ ሳሳት የመጣ ጥበብ አይደለም። ጳውሎስ እንዳለው፡- "ነገር ግን አስቀድሞ ከዘ መናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ እንናገራለን።" (ቁ. 7) ይህ ጥበብ ሥጋዊ የሆነ፥ ከአዕምሮ የመነጨ ፍልስ ፍና፣ አይደለም። ጳውሎስም "የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፣ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተፅፎአልና" ይላል። (1ቆሮ. 1፡19) የዚች ዓለም

ጥበብም አይደለም፤ ምክኒያቱም "ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለ ም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን? (1ቆሮ. 1:20)። ነገር ግን ይህ ጥበብ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው ። (1ቆሮ. 1:21፤24፤ 2:7)

➢ ሦስተኛ፡- ይህ ጥበብ እግዚአብሔር ልክብራችን የወሰነው ነው። (2:7) በሮሜ 5:2 ላይም "በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን" ይላል። እንዲያውም ጳውሎስ በ1ቆሮ. 2:9 ላይ "ዓይን ያላየችው (INVISIBLE) ፤ ጆሮም ያልሰማች ው (INAUDIBLE)፤ እና "በሰውም ልብ ያልታሰበው፤ (INCONCEIVABLE) ነው። "ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።" (2:10)

ሐዋርያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር በክርስቶስ፤ በመንፈስ ቅዱስም በኩል የተገ ለጠው ጥበብ ላይ በማጠንጠን የመንፈስ ቅዱስን ባህርያት በአራት ደረጃዎች ይገልጸዋል።

❖ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገርም እንኳን ሳይቀር ሁሉንም የመመ ርመር ሥልጣን አለው። (2:10-11)

❖ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ምሥጢር የመግለጥ ሥልጣን አለው። (2:10-12)

❖ መንፈስ ቅዱስ በመገለጥ (REVELATION) የመጣውን የእግዚአብሔርን ምሥ ጢር፤ የነቢያትና የሐዋርያትን ማስተዋል በመክፈትና በመምራት (INSPIRATION) የእግዚአብሔር ቃል እንዲፃፍ አድርጓል።(2:13) የነቢያትንና የሐዋርያትን ቃላት በመጠቀም የራሱን ቃል በሥልጣን ተናግሯል። የእግዚአ ብሔር ቃል ዋና ደራሲው መንፈስ ቅዱስ ነው።

❖ መንፈስ ቅዱስ በዘመናት ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔር ምሥጢር፤ በጽሑ ፍ እንዲፃፍ ካደረገ በኋላ፤ ትውልድም ሁሉ የቃሉን ምሥጢር በመግለጥ፤ በማስ ተማርና ማስተዋሉን በመክፈት (ILLUMINATION) ይለውጣል፤ ያሳድጋል፤ የጥበብም ባለጠግነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። (2:13-16)

❖ በጣም የሚገርመው ግን መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት እንድ ንችል አዕምሮአችንን የሚከፍት፤ የሚመራንም እርሱ ከሆነ በክርስቲያኖች፤ ይልቁንም በመሪዎች መካከል የሐሳብና የአሠራር ልዩነት በየጊዜው መከሰቱ ቆም ብለን እንድናስብ እንገደዳለን።

❖ የእግዚአብሔር ቃል ለህይወትም ይሁን ለአገልግሎታችን የመጨረሻው ሥልጣ ን እንደሆነ መቀበል አለብን።
✓ የእግዚአብሔር ቃል ዋና ዓላማ የክርስቶስን ማዕከላዊነት እንደሆነ መረዳት ይኖርብናል።
✓ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የአተረጓጎም መመሪያ ሊኖረን ይገባል።
✓ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ክርስቲያን ህብረተ ሰብ በአንድነትና በመደማመ ጥ በሥልጣኑ ሥር ተቀምጠን ልናጠናው ይገባል።
✓ የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት በፍፁም ትህትና፣ በተከፈተ ልብ፣ በቅንነ ትና ለመቀበል ከሚፈልግ መንፈስ ጋር ልንቀርብ ይገባናል። ለዓመታት የያ ዝናቸው የራሳችን ግላዊ አስተሳሰቦችን፣ ከባህላችን የወረስናቸው፣ (ከቤተ እምነት ወይም ካደግንበትሕብረተ ሰብ፣ የወረስናቸው፣ ከቃሉ ጋር የማይጣ ጣሙ ባህሎች) እና የግላችንን ስምና ዝና ለማስፋት ያለንን ንፁሕ ያልሆነ ረሃብ እንዲያስጥለን ልንፈቅድለት ይገባል።

## 6. የቤተ ክርስቲያን አሠራር:-

ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ያላቸው መረዳት የተበላሸ ካልሆነ በስተቀር አሁን የሚያሳዩትን ግርድፍና ያልተለወጠ ባህርይ ሊገል ፁና ሊያሳዩ እንደማይችሉ አስተውሏል። ይህንን ሐሳብ ለመግለፅ ሦስት ዓይነት የቤተ ክርስትያን ገፅታዎችን በማስቀመጥ በአመራር ላይ ከተቀመጡትም ይሁን፣ ለምዕመኑም ያላቸውን አንድምታ ያሳያል።

◆ አንደኛ የእርሻ ተምሳሊት "የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፣" (1ቆሮ. 3፡9)
◆ ሁለተኛው የህንፃ ተምሳሊት "የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፣" (1ቆሮ. 3፡9)
◆ ሦስተኛው የቤተ መቅደስ አሠራር ተምሳሊት "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" (1ቆሮ. 3፡16)

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲያውም ለቆሮንቶስ ሰዎች እጅግ የጠለቀና የሚያሳስብ ጥያቄ በፊታቸው ያቀርብላቸዋል:-

*"አጵሎስ እንግዲህ ምንድን ነው? ጳውሎስስ ምንድን ነው? በእነርሱ እጅ ያመና ችሁ አገልጋዮች ናቸው፣"* አጵሎስም ሆነ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሰዎች ላይ ሊሰለጥኑ የመጡ ሳይሆን፣ ሊያገለግሉ የመጡ አገልጋዮች ናቸው። የቆሮንቶስ ሰዎች የእምነታ

ቸው መዳረሻም ይሁን የእምነታቸው ምንጭ አይደሉም:: ነገር ግን የቆሮንቶስ ሰዎች በክርስቶስ ወዳለው ምክኒያት የሆነ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው:: ከዚህም ሌላ "ጌታ እንደሰጣቸው ያገለግላሉ::" የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠሩ መሣሪያዎች ናቸው::

- ❖ "*እኔ ተከልሁ፤*" (ቁ. 6)
- ❖ "*አጵሎስም አጠጣ፤*" (ቁ. 6)
- ❖ "ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር::" (ቁ.6)
- ❖ <u>ቤተ ክርስቲያንን በመሪዎቿ አንጻር ሳይሆን መተርጎም፤ ማጤንና መገምገም ያለብን፤ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን አኳያ መመዘን መለካትና መታየት አለባቸው</u>!!!
- ❖ ደግሞም ዓለም ቤተ ክርስቲያንን እንደ ኢንስቲቱሽንና መሪዎቿም በሰብዓዊ ሥልጣን የተሳበሱ "ዝነኞች" እንደሆኑ እንደምታስብ ልናስባት የእግዚአብሔር ቃል አይፈቅድልንም:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የጻነና በቃል ኪዳን የተጠራ አዲስ ሕበረተሰብና የእግዚአብሔር ክብር በዓለም ላይ ለማንጸባረቅና ለመግለጥ የተጠራች እንደሆነች ልናስብ ይገባናል::
  - ❖ *<u>ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ትምክህት፥ አለኝታ፥ እና ዓምድ፥ መሪዎቿ ሳይ ሆኑ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው</u>!!!*

> ❖ **<u>ክብር</u>**: -ለእግዚአብሔር አብ-የተዘራውን ማብቀልና ማሳደግ ለሚችለው፤
> - ለእግዚአብሔር ወልድ:- የቤተ ክርስቲያን አምድና መሠረት ለሆነው፤
> - ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ:- ለቤተ ክርስቲያን ሕይወትን እየሰጠ፤ በውስጧ ለሚኖርና ለሚቀድሳት ይገባል:: (1ቆሮ. 1:31፤3:21-23)

**7. የአገልግሎት ሞዴሎች:-** (1ቆሮ. 4: 1-21)

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እስከ አሁን የተከሰቱትን ጥግ የሆኑ አስተሳሰቦች አሉ:: በአንድ በኩል የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን (ፓስተሮች፤ ወንጌላውያን፤ ወዘተ) በላጭነት እንዳላቸው የሚያሳይ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን በጥብቅ የሚጻረር የትርፍ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡትን በላጭነት የሚያሳይ (ሽማግሌዎች፤ ዲያቆናት፤ ቦርድ፤ ወዘተ) ጥግ የሆኑ አስተሳሰቦች እንዳሉ የማይካድ ሐቅ ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ "አጵሎስ እንግዲህ ምንድን ነው? ጳውሎስስ ምንድን ነው?" (3፡ 5) ያለውን ልንመልሰው የሚገባ ጥያቄ ነው። በተጨማሪም በምዕራፍ 4:1 ላይ "እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋ ቢዎች ይቁጠረን" ይላል። የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ይሁኑ፣ የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች ከዚህ በላይም ሆነ፣ ከዚህ በታች ሊሆኑ አይችሉም። ለዚህ ነው ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሰዎች እጅግ ያዘነው። "እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፣ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፣ እኔስ የክርስቶስ ነኝ፣..." በማለት በግለሰቦች ዙሪያ መጠለላቸውና፣ ቤተ ክርስቲያን የግለሰቦች እንደሆነች መቁጠራቸው (የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ይሁን የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች) ከእውነት የራቀና ክርስቶስንም የማይወክል አጉል አመለካከት ነው።

- በአንድ በኩል የፓስተርነት (የመጋቢነት) አገልግሎት እጅግ የከበረ እንደሆነ የምናውቀው በ1ጢሞቴዎስ 3፡ 1-7 የተሰጠው መለኪያ ከፍተኛነት ስናይና፣ ጳውሎስ በ1ተሰሎንቄ 5:12-13 ላይ "*ወንድሞች ሆይ፣ በመካከላችሁ የሚደክ ሙትን በጌታምየሚገዙአችሁን የሚገሥጹአችሁንም ታውቁ ዘንድ፣ ስለ ሥራቸ ውም* <u>*በፍቅር*</u> <u>*ከመጠን ይልቅ ታከብሩአቸው ዘንድ እንለምናችኋለን*</u>*።*" ያለውን ቃል በምናይበት ጊዜ ነው።
- በሌላ በኩል ደግሞ ሚዛኑን ለመጠበቅ ጳውሎስ ስለ ራሱ፥ ስለ አጵሎስና ስለ ኬፋ (ጴጥሮስ) የሰጠውን መግለጫና፣ "*እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌ ዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቁጠረን።*" ያለውን ሐሳብ ማስተዋል ይኖርብናል። ፓስተሮችም ጳውሎስ ያለውን ቃል ልናስብ፣ ዋና የዓላ ማችን መዳረሻ አድርገን ልንወስድ ይገባል። እንዲህ የሚለው:-"*እንደዚህም ሲሆን፣ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈልጋል።*" (1ቆሮ. 4:2) እርስ በርሳችንም ከመፈራረድና የማይገባ ትችት ከመናገርም ልንቆጠብ ይገባ ል። "*ነገር ግን በእናንተ ዘንድ፣ ወይም በሌላ ሰው ዘንድ ብፈርድ ለእኔ ምንም አይደለም። እኔም በራሴ እንኳ አልፈርድም፣ በራሴ ላይ ምንም አላውቅምና።*" (4፡ 3) ጳውሎስ በመቀጠልም "...ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ አን ዳች አትፍረዱ።" በአንድ በኩል ለእግዚአብሔር ሥራ መጠራት እጅግ የከበረ ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ደግሞ መለኪያው ግን እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ እንደፈለ ጉ መኖር የሚቻልበት ኑሮ አይደለም።
- ፓስተሮች "*የእግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች*" ናቸው። (4፡ 1-2) ፓስተሮ ች በማስተማር ጸጋቸው (1ጢሞ 3:2)፣ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በመጠበ

ቃቸው፣ እና ለእግዚአብሔር ቃል እውነተኞችና ታማኞች በመሆናቸው "የእግ ዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች" ናቸው:: (4: 1-2)

❖ ፓስተሮች "*የክርስቶስ አገልጋዮች*" ናቸው (3: 5-9)

❖ ፓስተሮች "ለዓለም፥ ለመላእክትም፥ ለሰዎችም መጫወቻ" ናቸው:: (4: 8-13) ጳውሎስ እንዲያውም ሐሳቡን በማጥለቅ "*እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛል ና::*" (4: 9) በመቀጠልም ጳውሎስ "*...እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል::*" (4:13) ለዚህ ተቃውሞ ዋናው ምክኒያት የምንሰብከው ወንጌል በነፃ የተሰጠ ስጦታ አዳኝ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ የሚያበስርና፣ ቅድስ ናና የህይወት ለውጥ እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ ነው::

❖ ፓስተሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው አዲሱ ሕብረተ ሰብ "*አባቶች*" ናቸው:: (4:14-21) ጳውሎስ "*እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥጻችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ይህን አልፅፍም:: በመቀጠልም "በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖ ሩአችሁም ብዙ አባቶች የሉአችሁም*" ይላል:: (4፥ 15)

ይህንን ምዕራፍ ለማጠቃለል የእኛ አመራር ሞዴላችን ከተለያዩ ባሕሎች የወር ስናቸው፣ ወይንስ በእግዚአብሔር ቃል የምናየው የክርስቶስ የአገልጋይነት አመራር የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይገባል? ብለን ልንጠይቅ ግዴታ አለብን:: ምክኒያቱም በዓለ ም ላይ በተለያዩ ባሕሎችና አሠራሮች ሳናውቅውና ሳናስተውለው እንዲህ ዓይነቱ በከረረ መዋቅርና የግለሰቦችና ወይንም የቡድን ኃይልና ሥልጣን የሚያንጸባርቁ የአ መራር ስልቶች ሳይታወቀን በቤተ ክርስቲያን ላለን አመራር እያዋልነው እንዳይሆን ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው:: ከእነዚህም መካከል:-

- በአፍሪካ ውስጥ:- የነገድ አለቃ (TRIBAL CHIEF)
- በላቲን አሜሪካ ውስጥ:- የወንድ የበላይነት (MACHISMO - EXAGURATED MASCUALINITY)
- በሳውዝ ኤስያ ውስጥ:- በደቀ መዛሙርቱ የሚመለክ ጉሩ (GURU)
- በኢስት ኤስያ ውስጥ:- ማንም ሊቋቋመው የማይችለው ሥልጣን ያለው የኮንፊሽየስ አስተማሪ (THE CONFUCIAN TEACHER)
- በብሪትን ሕንድ ከእጃቸው ነፃ ከመውጣቷ በፊት (ከ 1947 ዓ. ም. በፊት) የነበረ:- የራጅ አስተሳሰብ (THE BRITISH RAJ MENTALITY)

❖ እነዚህ ሁሉ አስተሳሰቦች ግን "*ከእኔ ተማሩ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና::*" ካለው የጌታ መንፈስና ሐሳብ ጋር የማይሄዱና፤ እንዲያውም በቀጥታ የሚጋጩ ናቸው:: ከዚህ ይልቅ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችም ይሁን፤ የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች የሚከተሉትን ዐበይት ጉዳዮች ልብ ብለው ሊያስተውሉ ይገባል::

## <u>ትህትና</u>:-

- <u>በክርስቶስ ፊት</u>:- የእርሱ አገልጋዮች ስለሆንን፤
- <u>በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ፊት</u>:- ባለ አደራዎች ስለሆንን፤
- <u>በዓለም ፊት</u>:- ተቃውሞን የምንቀበል ስለሆንን፤
- <u>በቤተ ክርስቲያን ምዕመን ፊት</u>:-ልናገለግለው የተጠራንለት ስለሆነ!!!

# ክፍል አራት

## የአመራር ሥነ መለኮታዊ እሳቤ

# ምዕራፍ ስምንት

## የአመራር ሥነ መለኮታዊ እሳቤ
## (THEOLOGICAL CONCEPT OF LEADERSHIP)

- *"የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፤ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፤ ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፤ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።" (1ቆሮ. 12፡4-6)*
- *"ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፤ ይመግበዋል፤ ይንከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፤ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ" (ኤፌ. 5፡29-33)*
- *"አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና .... ነገር ግን ብልቶች እርስ በርሳቸው በትክክል ይተሳሰቡ ዘንድ እንጂ በአካል መለያየት እንዳይሆን ለጎደለው ብልት የሚበልጥ ክብር እየሰጠ እግዚአብሔር አካልንአገጣጠመው።" (1ቆሮ. 12፡12-30)*

ባለፉት ዘመናት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል መለያየት፣ መገፋፋትና መጠላላት እየበዛ መምጣቱ በእነርሱ የሚገለገለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ሳይፈልግ ለአመራር ያለው አክብሮት እየቀነሰ በመምጣቱ ራሱን መስቀለኛ መንገድ ላይ እን ዲያስቀምጥ አድረጎታል። ከዚህም ሌላ ቤተ ክርስቲያን በውጭው ዓለም ላይ የነበራት አዎንታዊ ተጽዕኖ እየደበዘዘ በመሄዱና፤ ትንቢታዊ ድምጿም ለማሰማት ካለመቻ

ልዋም በላይ፣ የአንዳንድ መሪዎች ሞራላዊና ሥነ ምግባራዊ መለኪያቸው ዝቅተኛ እየሆነ መምጣቱም የሚያሳስብ ነው። ይህ ሁኔታ አዲሱ ትውልድም የመጣ እንግዳ ነፋስ የሚውስደው፥ ለራሱ ትውልድ ቅንዓት የሌለውና፥ የወደፊት ራዕይና ተስፋው እየደበዘዘ የመጣ እንዲሆን አድርጎታል።

በቤተ ክርስቲያን ጓዳ ውስጥ የሚታይ የነበረው ችግር የአደባባይ ቁስል እየሆነ በመምጣቱ ምክኒያት በሌላ የወንጌል ሥራ ላይ ልናውለው የነበረውን ኃይል፣ ችግሮችን በመፍታት፥ በመሪዎች መሀል እርቅ እንዲመጣ በመታገልና፥ የምዕመንም መንፈስ እንዲጠበቅ ለማረጋጋት በመሞከር ዘመናችን እንድናሳልፍ አድርጎናል። <u>ይህ ሁኔታ አሳሳቢ እየሆነ በመሄዱ ምክኒያት የቤተ ክርስቲያንን ደህንነትና አንድነት ለማየት የሚጓጉ ሁሉ የችግሩ መንሳኤ ምን እንደሆነ ለማወቅ በእግዚአብሔር ፊት ከብዙ እንባ ጋር በጸሎት መቅረባቸው አልቀረም። በተቀደሰ አዕምሮም በርካታ ጥያቄዎችን በማንሣት እንቅልፍ ያጡባቸው ሌሊቶች ቀላል አይመስሉኝም።</u> የችግሩ ምክኒያት ፡- <u>የመተዳደሪያ ደንብ ጥራት ማጣት</u>? <u>የውስጠ ደንብ አለመኖር</u>? <u>የመዋቅር ግልፅነት ማጣት</u>? <u>የአሠራር አለመጣጣም</u>? <u>ወይንስ የያዝነው ሥነ መለኰታዊ እሳቤ የተሣሣተ፥ የተዛባና፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ፥ "የቤተ ክርስቲያን ባሕላዊ አሠራር" (CHURCH TRADITION) ላይ የተመሠረተ፥ ወይንም ደግሞ ከውጭው ዓለም የተወሰደ ስለሆነ የመጣ ችግር ነው</u>? የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳታችን መፍትሔውንም ለማግኘት ይረዳናል ብዬ አምናለሁ።

የመተዳደሪያ ደንብ ጥራት ማጣት፣ የውስጠ ደንብ አለመኖር፣ የመዋቅር ግልፅነት የሌለው መሆኑና የአሠራር አለመጣጣም ችግሩ ለመባባሱ ምክኒያት መሆናቸውን በከፊል ባምንበትም፣ በእኔ አመለካከት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለው የአመራር ችግር ዋናው መነሻ <u>ስለ አመራር ያለን የሥነ መለኰት እሳቤ የተሳሳተ፥ የተዛባና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ በመሆኑ የመጣ ነው</u>!!! የሥነ መለኰት እሳቤአችን ሳይለወጥ ችግሩን የመተዳደሪያ ደንብ በመለወጥ፣ የውስጠ ደንብ በማውጣት፣ የመዋቅር ግልፅነት እንዲኖር በማድረግ፣ ወይንም አሠራር በማመቻቸት ይፈታል ብዬ አላስብም። እንግዲህ የሥነ መለኰት እሳቤአችን ምን መሆን አለበት? መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ እሳቤ እንዲኖረን ለማድረግ የሚረዱ ሞዴሎች አሉ ወይ? የሚኖረን የአመራር ሥነ መለኰት እሳቤ በአመራራችንም ሆነ ስለ ሌሎች መሪዎች ባለን አመለካከት ምን ያህል ተጽዕኖ ይኖረዋል?

የቤተ ክርስቲያን የአመራር ሥነ መለኮት እሳቤ እንዲኖረን የሚረዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆኑ ሞዴሎች መካከል ሦስቱን በማቀርብበት ጊዜ የጠለቀ ሚስጢራዊነታቸውን ከመገንዘቤ የተነሣ በፍፁም ትሕትናና የእውቀት አድማስ ውስንነቴንም በማስተዋል እንዳቀረብኳቸው ለአንባቢዎች ለመግለፅ እወዳለሁ:: እነዚህም የአመራር መለኮት እሳቤዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- "የጋብቻና ቤተሰብ ሥነ መለኮት"
- "የክርስቶስ አካል ሥነ መለኮት"
- "የሥላሴ ምስጢር ሥነ መለኮት"

እነዚህ ሦስት የአመራር ሥነ መለኮት እሳቤዎች በሰፊው ከማየታችን በፊት የሥነ መለኮት ምንነት፥ በሥነ መለኮትና በአመራር መካከል ያለውን ግንኙነት፥ እና የአመራር እሳቤ በሥነ መለኮት ላይ የተመሠረተ ሲሆንና ሳይሆን ያለውን ልዩነት መዳሰሳችን ይገባል ብዬ አምናለሁ:: ምክኒያቱም ሑክማን፣[90] ኖርዝሐውስ፣[91] እና ዩክል፣[92] የሚባሉ ጸሐፊዎች በየግላቸው ባደረጓቸው ጥናቶች አመራር ሥነ መለኮትን የማያካትት እንደሆነ ያመለክታሉ:: ስለዚህ የአመራር ሥነ መለኮት ለመረዳትና ሊኖረን የሚገባ የሥነ መለኮት እሳቤ ለማወቅም መጠነኛ በሆነ መልክ ማየት አስፈላጊ ነው::

አመራርን በተመለከተ በተደረጉት ብዙ ጥናቶች፣ ከጥናቶቹም በወጡት የሐሳብ ዕድገቶችና መነሻ አድርገው በወሰዷቸው ዘዴዎች ሥነ መለኮትን የሚያካትቱ እንዳልነበሩ በዓመታት መሃል የተከሰተ ሐቅ ነው:: አንዱም ምክኒያት ሥነ መለኮት "የእግዚአብሔር ሐሳብና ዓላማ" የሚጠናበት ጥናት በመሆኑና፣[93] አመራር ደግሞ ሰው ተኮር የሆነ በሥነ ሰብዕ (ANTHROPOLOGY)፣ በሥነ ማሕበረ ሰብ (SOCIOLOGY) እና በሥነ ልቦና (PSYCHOLOGY) ጥናት ላይ የተመሠረተ በመ

[90] Gill R. Hickman, *Leading Organizations: Perspective for a New Era*,(Thousand Oaks, CA: Sage, 1998).
[91] Peter G. Northouse, *Leadership: Theory and Practice*, (Thousand Oaks, CA: Sage, 2004).
[92] Gary Yukl, *Leadership in Organization,* 5th. ed., (Upper Saddle River, NJ: Pretice Hall, 2002).
[93] Millard Erickson, *Christian Theology*, (Grand Rapids, MI: Baker Books, 1985).

ሆኑ ነው::[94] ጋሬት የሚባለው ጸሐፊ የሥነ መለኮት ትርጉም ወሰን ሲጽፍ "ሥነ መለኮት በእግዚአብሔር ሐሳብና ዓላማ ላይ ያተኮረ ጥናት ነው"[95] ይለዋል::

በሌሎች መስኮች እንዳለው ጥናት የሥነ መለኮት ጥናትም እንደዚሁ ህብረ ብዙ እንደ ሆነ የሥነ መለኮት ምሁራን ካደረጓቸው ጥናቶች ማየት ይቻላል:: አንዳንዶች ሥነ መለኮትን ከታሪካዊ እይታ ብቻ በማየት በዓመታት መሃል የተነሡትን የሥነ መለኮት ምሁራን የጻፏቸውን ብቻ የሚመለከቱ አሉ::[96] ሌሎች ሥነ መለኮትን ከፍልስፍና አንጻር በማየት የእግዚአብሔርን ነገር ለመረዳት ይሞክራሉ::[97] ካርሊን በዚህ መጽሐፉ ይህ የሥነ መለኮት ጥናት ከታሪክ፣ ከፍልስፍና፣ ከሥነ አመክንዮ፣ ከሕግ፣ እና ከሌሎች ጥናቶች በማጠናቀር እግዚአብሔርንና ሥራውን ለማየት ያስችላል[98] ብሎ ያምናል:: እንዲህ ዓይነቱ ጥናት ግን መጽሐፍ ቅዱስን መነሻና መሠረት አድርጎ ሳይወስድ እግዚአብሔርንና የእግዚአብሐርን ጉዳይ ለማጥናት መሞከሩ የሥነ መለኮት ጥናት ለማለት ያስቸግረኛል::

ከእነዚህ አቀራረብ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ስለ ራሱ፣ ማለትም እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ጥልቅ ዓላማ መናገር ስለሚችል የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተረጉመው በመፍቀድ የሚደረገው ጥናት በፍፁም ትሕትናና ቅንነት፣ ከፍትነትና መታዘዝ ብንይዘው ትክክለኛውን ሥነ መለኮት ለማግኘት እንደሚረዳን ሙሉ እምነት አለኝ:: እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት በዓመታት መካከል እያደጉ የመጡ የሉተር÷ የካልቪን÷ የሪፎርምድ÷ የአርሚንያን÷ የካቨናንት÷ የዲስፔንሰሽናል÷ የሥነ መለኮት ዓይነቶች እንዳሉ ብናውቅም፤[99] ሁሉም ዋና መሠረታቸው አድርገው የተነሡት መጽሐፍ ቅዱስን ነው::

ስለዚህ ስለ አመራር መረዳት ትክክለኛ በሆነ መሠረት ላይ መቆም ስላለበት የሥነ መለኮት እሳቤ ሊኖረን ይገባል:: እዚህ ላይ ሁለት ጥግ የሆኑ አመለካከቶች

---

[94] Robert Layton, *An Introduction to Theory in Anthropology*, (Cambridge, UK: Cambridge University Press, 1998).
[95] James Leo Garrett, *Systematic Theology*, vol. 1-2, 3rd. ed., (Grand Rapids, MI: Baker Academic, 2007).
[96] Charles Hodge, *Systematic Theology*, vol.1 (1872, reprinted), Oak Harbor, WA: Logos Research Systems, Inc., 1997), 1-2.
[97] Paul S. Karleen, *The Handbook to Bible Study: With Guide to the Scofield Study System,* (New York: Oxford University Press, 1987).
[98] Ibid.
[99] Paul P. Enns, *The Moody Handbook of Theology*, (Chicago, IL: Moddy Press, 1997, c.1989).

እንዳሉ ለመግለፅ እፈልጋለሁ:: በአንድ በኩል በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችና ሴሚናሪ ዎች ውስጥ ያለው የአካዳሚክ ትምህርት አሰጣጥ በሥነ መለኮት ጥናት ላይ ያተኩ ረ ሆኖ፤ ብዙዎቹ ሴሚናሪዎች የአመራር ጥናት የማይሰጡ ከመሆናቸው የተነሣ፤ ተመራቂዎቹ ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ የተማሩትን በሥራ ለመተርጎም የማ ይችሉና በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ሲቀመጡ ግራ ሲጋቡ ማየት ከጀመርን ቆይ ተናል:: በአንፃሩ ደግሞ አመራርን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ስላልተመሠረተ፤ ከውጭው ዓለም የተወሰዱ፤ የሥነ መለኮት መሠረት የሌላቸው እሳቤዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን በማምጣት፤ መሪዎች የክርስቶስ አካል የሆነችውን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን "ሊቆጣጠሩና በመጫን ለመግዛት ሲሞክሩ" ማየቱ የሥነ መለኮት እሳቤ ያለህ ያሰኛል::[100]

ዌልች ባርናና ስኬዋርትዝ በስፋት ያጠኗቸው ጥናቶች የሚያሳዩት የሥነ መለ ኮት ትምህርት ለብቻ እንደማይበቃና የአመራር ጥናትንም ሊያካትት እንደሚገባ አስረግጠው በጽሁፍ ሥራቸው ገልጠዋል::[101] እንዲያውም ስኬዋርትዝ የተባለው ጸሐፊ ከአንድ ሺ ቤተ ክርስቲያኖች በላይ በመውሰድ ባደረገው ዓለም አቀፍ ጥናት የአካዳሚክ የሥነ መለኮት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ዕድገትና በአብያተ ክርስቲ ያናት ጥራት ያመጣው ሰበብ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው አረጋግጧል::[102] የዚህ አሉ ታዊ ትጽዕኖ ምክኒያት ፓስተሮች የአመራር ጥራትና ብቃት ሳያሳዩ በማስተማርና የዶክትሪን ጥናት ብቻ በማስጨበጥ ላይ በማተኮራቸው ነው ብዬ አስባለሁ::

በአንፃሩ ደግሞ ምንም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችና ሴሚናሪዎች የሚሰ ጠው ዘርፈ ብዙ የሆነ የሥነ መለኮት ትምህርትና የአመራርን ጥናት የማያካትት መሆኑ ቢታወቅም፤ በአመራር ላይ የተደረጉ ጥናቶች የሚያመለክቱት የሥነ መለኮ ት ይዘት የሌለው፤ ቅርጽ ብቻ እየሆነ መምጣቱ እጅግ የሚያሳስብ ነው::[103] እውነቱ ግን በመሪዎች ሕይወትና አገልግሎት የሞራልና የሥነ ምግባር መለኪያ ደብዛው እየጠፋ መምጣቱ፤ በመሪዎች ላይ የሚታየው ራስ ተኮር (EGO-CENTRIC) የሆነ

---

100 See Robert H. Welch, *Church Administration: Creating Efficiency for Effective Ministry,* (Nashiville, TN: Broadman & Holman Publishers, 2005);

101 Ibid.; George Barna, ed. *Leaders On Leadership: Wisdom, Advice, and Encouragement on the Art of Leading God's People, The Leading Edge* Series, (Ventura, CA: Regal Books, 1997); Christian A. Schwarz, *Natural Church Development,* (St. Charles, IL: Church Smart Resources, 1996).

102 Schwartz, *Natural Church Development*, 1996.

103 See Northouse, *Leadership and Practice,* 2004; Yulk, *Leadership in Organizations*, 2002.

አካሄድ እየተከሰተ መታይቱ፥ በመሪዎች መካከል የሚታየው ውስጣዊ መገፋፋት የአደባባይ ምስጢር እየሆነ መምጣቱና፥ በአገልጋዮች ሕይወት ውስጥ የሚታየው የጠለቀ የባሕርይ ችግር እየጐላ መሄዱ የሚያመለክተው፣ አመራር የሥነ መለኮት ይዘት የሌለው፥ ቅርፅ ብቻ እንደሆነ ነው::[104]

ይህንን ሐሳብ ለማጠቃለል ሥነ መለኮትና አመራር አንድ ላይ አብረው የሚሄዱ ናቸው:: ሥነ መለኮት የሌለው አመራር በሴኩላሩ ዓለም በተገኙ ንድፈ ሐሳቦች (THEORIES) ብቻ ሲመሠረት፣ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆኑ አሠራሮችን ወደ ቤተ ክርስቲያን በማምጣት ምዕመን እንዲታመስ የሚያደርግ ይሆናል:: በሌላ በኩል ደግሞ አመራርን የማያካትት የሥነ መለኮት ጥናትም ባሳደጓቸው ነባር መሪዎችና ባሳደገቻቸው ቤተ ክርስቲያን ላይ ለችግሮች መነሳት ምክኒያት የሚሆኑና፣ የአመራር ችሎታ የሌላቸው ሰዎችን የሚያፈራ ስለሚሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳትን የሚያመጣ ይሆናል::

ስለዚህ "የጋብቻና ቤተሰብ ሥነ መለኮት" "የክርስቶስ አካል አሠራር ሥነ መለኮት" እና "የሥላሴዎች ምስጢር ሥነ መለኮት" ለአመራር ያላቸው ሞዴልነት ማየታችን እጅግ ወሳኝ ነው!!!

## I. የጋብቻና ቤተሰብ ሥነ መለኮት

## (THEOLOGY OF MARRIAGE AND FAMILY)

### ሀ. መግቢያ:-

የጋብቻና ቤተሰብ ሥነ መለኮት ለማጥናት በምንጀምርበት ጊዜ "*በመጀመሪያ እግዚአብሔር*-...." (ዘፍ. 1:1) በሚለውና "*በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር::*" (ዮሐ. 1:1) የሚለውን ሐሳብ

[104] See Les Carter and Jim Underwood, *The Significance Principle*, (Nashiville, TN: Broadman and Holman, 1998); Kevin Cashman, *Leadership from the Inside Out*, (Provo, UT: Executive Excellence, 1998); Richard Foster, *Money, Sex, and Pwer,* (San Francisco, CA: Harper & Row, 1985); John W. Gardner, *Self Renewal: The Individual and the Innovative Society,* (New York: Harper & Row, 1963); Os Guiness, *Character Counts,* (Grand Rapida, MI: Baker Books, 1999); James M. Kouzes and Barry Z. Posner, *Credibility*, (San Francisco, CA: Jossey-Bass, 1993); Gordon McDonald, *Ordering Your Private World,* (Nashville, TN: Thomas Nelson, 1985); Gary L. McLntosh and Samuel D. Rima, Sr. *Overcoming the Dark Side of Leadership,* 2000; Michael R. Milco, *Ethical Dilemmas in Church Leadership*, (Grand Rapida, MI: Kregel, 1997); Thomas J. Stevenin, *People Power,* (Chicagi, IL: Northfield, 1996).

ልንጀምር ይገባል ብዬ አምናለሁ:: ምክኒያቱም በፈጣሪንቱ ጋብቻና ቤተሰብን የፈ ጠረው ይሁን፣ በአዳኝነቱ ደግሞ ጋብቻና ቤተሰብን የሚያቆየውም እግዚአብሔር ነው:: በፍጥረት ጊዜ "*ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፣ ...እግዚአብ ሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፣ ውንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው::*" (ዘፍ. 1:26-27) ያለው እግዚአብሔር፣ በቤዛነት ጊዜ ደግሞ: "*አስቀድሞ ያውቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናአልና::*" (ሮሜ 8:29)

"*በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ::*" (ዘፍ. 1:1) ከሚለው ሐሳብ በመነሣት ማሰብና ማወቅ ያለብን እውነቶች መግለፁ አስፈላጊ ነው:: አንደኛ እግዚአብሔር ከጊዜ በፊት ዘላለማዊና ልዓላዊነት ያለው አምላክ ነው:: እግዚአብሔ ር በሦስቱ ስብዕናዎች፣ ማለት እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብ ሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ሆኖ በዘላለም ውስጥ የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር አምላ ክ ነው:: (ዘፍ. 1:1-3) ምሳሌ 8:22-23፣30-31፣ መዝ. 104:30፣) ሁለተኛ:- እግዚአ ብሔር በራሱ የተወሰነ አምላክ ሳይሆን በጊዜ ውስጥ ፍጥረታትን የፈጠረ፣ በራሱ ፈቃድም ካለ መኖር ወደ መኖር እንዲመጡ ያደረገ ነው:: "በመጀመሪያ እግዚአብ ሔር ሰማይናና መድርን ፈጠረ፣" በሚልበት ጊዜ ሰውን የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ አድ ርጎ "በምሳሌአችን እንፍጠር" እንዳለው ሰውን በመልኩ የፈጠረውም እግዚአብሔር ነው:: ከዚህም በላይ "እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መል ክ ፈጠረው፣ ውንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው::" የሚለው ሐሳብ በአንድነትና በነጠ ላነት በየግላቸውም እንዲሆኑ ፈጥሮአቸዋል:: ወንድና ሴት በጋብቻ የግንኙነት ጥምረት/ሥምረት በሚሆኑበት ጊዜ በግላቸው ያላቸው ስብዕና አንዱ በሌላው ተው ጧል ማለት አይደለም:: በአንድ ላይ እንደ ባልና ሚስት እግዚአብሔርን ሊያመልኩ ት ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም:: አንድም ናቸው፣ ሁለትም ናቸው::

ሦስተኛ:- የወንድና የሴት፣ በሌላ አንጋገር የባልና የሚስት የመኖራቸው ምክኒ ያትና የዓላማቸው መዳረሻ፣ የመኖራቸውም ዋስትና እግዚአብሔር ነው:: አራተኛ:- "እግዚአብሔርም ባረካቸው፣ እንዲህም አላቸው - ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ፤" (ዘፍ. 1:28) በሚልበት ጊዜ ለተለየ ዓላማ ካልሆነ በስተቀር፣ ልጆችን በመስጠት የሚባርካቸውም እግዚአብሔር ራሱ ነው:: እንደ እንስሶች÷ አዝርዕቶችና÷ ፍራ ፍሬ ዎች÷ ሰውንም ከአንዱ ዘር እንዲራቡ ሳይሆን እግዚአብሔር ያደረገው፣ እያንዳንዱ ልጅ ሲወለድ የተለየ ስብዕና (UNIQUE PERSONALITY) እንዲኖረው አድርጎ

መፍጠሩ፣ የመፍጠር ችሎታው ቀጣይነት እንዳለው ያመለክታል:: በብዙ አድናቆት ና ፍፁም መሰጠት ባለው አምልኮ እንድናስበው የሚገባን አንዳችን ከሌላችን ጋር የማንመሳሰል አድርጎ መፍጠሩን ነው:: በሌላ በኩል በዘመናችን እንደምናየው ባል ሚስት የግላቸውን የኑሮ እርካታ ፍለጋ ማሳደድ ሳይሆን፣ ከራሳቸው አልፈው ለሚ ተኳቸው ትውልድም ለመውለድና ለማሳደግ መብታቸውም፣ ግዴታቸውም ነው::

አምስተኛ:- እግዚአብሔር "ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም" (ዘፍ. 1:28) "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም፣ ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው::" በሚልበት ጊዜ ሰው (ወንድም ሆነ ሴት) እንደ ባልና ሚስትም ሆነ በየግ ላቸው እግዚአምሔር የፈጠራትን ምድር የማበጀት፣ የማስተዳደርና እንደ ባለ አደ ራ የመጠበቅም ኃላፊነት እንዳለባቸው ያመለክታል:: በአንድ በኩል አዲስ ነገር ለመ ተለም የሚያስችል ነፃነት አላቸው:: በሌላ በኩል የመጠበቅ ኃላፊንት አላቸው::

ስድስተኛ:- *"እግዚአብሔር አምላክም አለ÷ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት::"* የሚለው ሐሳብ ለተለየ ዓላማ ካልሆ ነበስተቀር የሰው ብቸኛ/ነጠላ መሆንን የማይወድ የግንኙነት ሥምረት/ጥምረትን የሚፈልግ አምላክ መሆኑን ያሳያል:: የመጀመሪያው የኃጢአት ውድቀት የመጣው ም"አዳምና ሔዋን" ለማናውቀው ምክኒያት ለብቻ በነበሩበት ወቅት እንደነበረ ልናስ ተውል እንችላለን:: (ዘፍ. 3:1-24)

ሰባተኛ:- ኃጢአትና ክፉ (EVIL) የክፋት ምንጭ ከሆነ ከሰይጣንና ሰውም በፈ ቃዱ ለሰይጣን ማታለል ራሱን አስልፎ በመስጠቱ ምክኒያት የመጣ እንጂ፣ የኃጢአ ትም ሆነ የክፉ፣ የዚህም ስበብ የሆነው የመከራና የሥቃይ ምንጭ እግዚአብሔር አይደለም:: እግዚአብሔር በኤደን ገነት ውስጥ "መልካማና ክፉን የሚያስታውቀው ን ዛፍ" ማብቀሉ ሰው በፈቃዱ እንዲያመልከው ለሰው የሰጠውን ፈቃድ ለማክበር ያደረገው ነው:: እግዚአብሔር ከሌሎች ሁሉ ፍጥረታት ለይቶ ለሰው ፈቃድ ሰጥቶ ታል:: በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ፣ እግዚአብሔር ለሰው የደህንነት መንገድ በፈጣሪነቱና በአዳኝነቱ ማዘጋጀቱ ነው::[105] (ዘፍ 3:15)

[105] See Karl Barth, *Church Domatics, III.1,* ed. by G. W. Bromiley and T. F. Torrance, (Edinburgh: T & T Clark, 1969); Ray Anderson and Dennis B. Guernsey, *On Being Family: A Social Theology of the Family*, (Grand Rapids, MI: Eerdmans Publication, 1985); Edwin H. Fieldman, *Generation to Generation: Family Process in Church and Synagogue*, (New York: Guilford, 1985), 19-39.

## ለ. የእግዚአብሔር ትኩረት በቤተሰብ ላይ፡-

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያቸውን ትውልዶች በሦስት ትውልዶች ልናጠቃልላቸው እንችላለን።

- የአዳምና ሔዋን ትውልድ (ዘፍጥረት 1-11)
- የአብርሃምና ሣራ ትውልድ (ዘፍጥረት 12 - ሚልኪያስ 4)
- የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ (አዲስ ኪዳን - ቤተ ክርስቲያን)

በሦስቱም ትውልዶች የምናየው አንድ ቁልፍ የሆነ ሐሳብ፣ የእግዚአብሔር ትኩረት በቤተሰብ ላይ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር በፍጥረት ጊዜ ሰውን በመልኩና በምሳሌው ከፈጠረ በኋላ፣ አዳም ብቻውን መሆኑን አይቶ "ለእርሱ ረዳት የምትሆነውን እንፍጠርለት" ሲል እናያለን። አንድም አዳም የውጭውን ዓለም (ምድርን) ከማስተዳደሩ በፊት በገዛ ቤቱ የአመራር ችሎታ እንዲኖረው ማድረጉን ስንመለከት፣ አንድም ደግሞ ሔዋን የእርሱ "ረዳት" እንድትሆን መስጠቱ፣ ያላየውንና ያላስተዋለውን ማስተዋል እንዲችል የምትረዳው እንደሆነች እንጂ፣ የእርሱ የበታች ወይም ተገዢ እንድትሆን የተሰጠች አልነበረችም። <u>እንደዚሁም አዳም (ወንድ) የቤተሰቡ መሪ ሆኖ ሚስቱን፥ ሔዋንም ሆነ የሚወለዱትም ልጆቹን በአመራሩ ሊያስተዳድራቸው መቻሉ በፍጥረት ጊዜ የተሰጠ እውነት እንጂ፣ ከውድቀት በኋላ የመጣ የኃጢአት ሰበብ ምክኒያት የተሰጠ እንዳልሆነ ልናስተውል ይገባል።</u>

1. እዚህ ላይ ልናውቀው የሚገባው እግዚአብሔር የነበረውን ዓላማ የጀመረው አንድን ቤተሰብ (አዳምንና ሔዋንን) በማስነሣት እንደነበረ ነው። ነገር ግን የመጀመሪያው ቤተሰብ የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳርፍ አልሆነም። እንዲያውም፡-

- ዘፍጥረት 3፡- የግለሰብ ኃጢአት፣
- ዘፍጥረት 4፡- የቤተሰብ ኃጢአት፣
- ዘፍጥረት 5-11፡- የሕብረተ ሰብ ኃጢአት

አዳምና ሔዋን በየግላቸው የሠሩት ኃጢአት፣ ቤተሰባቸውን ሲያፈርሱ ስናይ፣ ቤተሰቡ ደግሞ የሞራልና የሥነ ምግባር መለኪያ የሌለው ሕብረተ-ሰብ ሲሆንና በኃጢአት ከመበስበሱ የተነሣ እግዚአብሔር "ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ" ብሎ ሲናገር እናየዋለን። (ዘፍ. 6፡5-6) ሕብረተ-ሰቡ እግዚአብሔርን ለማስቆጣት በቤተሰቡ ያሳይ የነበረው ኢሞራላዊና ኢሰብአዊ የሆነ አመራር በአደባባይም በመግለፅ ሁሉንም ጨፍልቆ አንድ የማድረግ አሠራር (UNIFORMITY) እንዲኖር ለማድረግ እንዲያመች፣ ሰማይ ጠቀስ የሆነ ሕንፃ ሲሠሩ በድንጋይ ሳይሆን በጡብ ሲሠሩት እንመለከታለን።

ከዚህም ሌላ በልዩነታቸው ውስጥ አንድነታቸውን ከመጠበቅ ይልቅ፣ ለአገዛዝ እንዲ ያመቻቸው ቋንቋቸውን አንድ ሲያደርጉ ማየት በዘመናት መካከል ከተከሰተውና ከሚከሰተው የታሪክ እውነት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ልንገነዘብ እንችላለን። እንዲያውም ቤተሰብ ከመፍረሱ የተነሣ እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ጉዳይ ከነበ ራቸው የኑሮ ዘይቤ ሲያስወጡና የራሳቸውን ስም ለማስጠራት ሲታገሉ ማየት የሚገርም ትዕይንት ነው። (ዘፍ. 11፡1-9)

2. እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ያስነሣው ሁለተኛው ትውልድ የአብርሃምና የሣራ ትውልድ ነው። አሁንም ቢሆን የእግዚአብሔር ትኩረት ቤተሰብ እንደነበረ ልናስተውል እንችላለን። እላይ እንደተመለከትነው የባቤል ሕዝብ የራሱን ስም ለማ ስጠራት ይታገል እንደነበረው ዓይነት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባቸው ቃል ኪዳኖች መካከል "...<u>ስምህንም አከብረዋለሁ</u>፣...." (ዘፍ. 12፡1-3) የሚለው ሐሳብ እንዴት የጸንናና እውነተኛ ነው። እግዚአብሔር አብርሃምና ሣራን በሚያስነ ሣበት ጊዜ "የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፣" ብሎ ሲናገረው፣ ከዚህ ቤተ ሰብ ያለፈ የእግዚአብሔር ጥልቅ ዓላማ እንደነበረ ያሳያል። እዚህ ላይ መጠቀስ ያለ በት እግዚአብሔር በአይሁድ ሕዝብ ላይ የነበረው ዓላማ ስላልሆነለት፣ እኛ አህዛብ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ያሰበን ሳንሆን፣ ከመጀመሪያውም በነባራዊ ዓላማው ውስጥ የነ በርን እንደሆን ሊታወቅ ይገባል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሐሳብ በማፅናት "በአ ንተ አህዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ" ይላል። (ገላቲያ 3፡8) ስለዚህም እግዚአብሔር "ለምድር ነገዶች ሁሉ" በረከትና ሞዴል እን ዲሆኑ አብርሃምንና ሣራን አስነሣ። አሁንም ቢሆን ትኩረቱ በቤተሰብ ላይ ነው።

ይሁን እንጂ አብርሃምና ሣራ የቤተሰብ ሞዴል ሊሆኑባቸው ያልቻሉ ሁኔታዎ ች እንደነበሩ ከዘፍጥረት 16፡1-6 እና ከዘፍጥረት 20፡1-18 ባሉት ክፍሎች ማየት ይቻላል። እንዲያውም እግዚአብሔር ስለ አብርሃም ሲናገር "*ጽድቅንና ፍርድን በማ ድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና <u>ከእርሱ በኋላ ቤቱን እን ዲያዝዝ አውቃለሁ።</u>*" (ዘፍ. 18፡19) ይላል። የአብርሃም ልጅ የነበረው ይስሃቅም ርብቃን ካገባ በኋላ በልጆቻቸው ምክኒያት በዘመናቸው ሁሉ የግል ፍላጎት ግጭት እንደነበራቸው እንመለከታለን። (ዘፍ. 24፡33) በመካከላቸው የነበረው አለመግባባት ወደ ልጆቻቸው የተላለፈ ይመስላል። ይህ ሁኔታ በቀላሉ የማይገመት በትውልዶች ላይ ጠባሳ ጥሎ ከማለፉም ሌላ፣ በሁለቱም የወንድማማች ትውልዶች መሃል በቀልና ቁርሾ ለመካሄዱ ምክኒያት ሆኖአል። እግዚአብሔርም ከረዥም ዘመናት በኋላ እንኳ

ነቢዩ አብድዩን አስነሥቶ ይህንኑ ነባራዊ ችግር ሲጠቅሰው እናያለን። (ትንቢተ አብድዩ 1:1-21)

ከአባቶች መካከል ሦስተኛው የነበረው የይስሃቅ ልጅ ያዕቆብ ነው። ያዕቆብ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን የጋብቻ መለኪያ (ማለትም አንድ ባል ለአንዲት ሚስት) ሰብሮ አራት ሚስቶችን ካገባ በኋላ አሥራ ሦስት ልጆችን ወልዷል። (አሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶችና አንዲት ሴት ልጅ) በዚህ መሃልም ያዕቆብ ልጆቹን ለመምራት፣ ለማሳደግና በሥርዓት እንዲሄዱ ለማድረግ የሚችልበት የአባትነት የፍቅር ብርታት ኖሮት ልጆቹን ዲሲፕልን የማድረግ አቅም አልነበረውም። ከዚህም የተነሣ አሥሩ ወንድማማች በትንሹ ወንድማቸው በዮሴፍ ላይ ከጥላቻ አልፈው በጉድጓድ ወደ መጣል፣ ከጉድጓድ መጣል ለግብፃዊው ለጲጥፍራ ሲሸጡት እያየ ይህንን ለማቆም የሚችልበት የአባትነት አቅም አልነበረውም። ያዕቆብ ራሱ "*ልጅ አልባ አስቀራችሁኝ...ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ደረሰ።*" (ዘፍ. 42:36) ያዕቆብ ለፈርዖን አለው:- "*የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሠላሳ ዓመት ነው፤ የሕይወቴም ዘማናች ጥቂትም ክፉም ሆኑብኝ።*" ብሎ ሲደመድም፣ በንግግሩ ውስጥ ብዙ የህሊና ወቀሳም ሳይኖርበት አይቀርም።[106]

የብሉይ ኪዳንን መጽሐፍት በምንዳስስበት ጊዜ ባሎች ከአንዲት ሚስት ጋር ከመኖር ይልቅ ተጨማሪ ሚስቶች ማግባትን፣ በጋብቻ ውስጥ ፍቺ እየበዛ መሄዱን፣ ከጋብቻ ውጭ ዝሙትና ርኩስት እየሰፈነ መምጣቱን፣ በእስራኤል ሕዝብ መካከል ሰዶማዊነት እየታየ መምጣቱን (መሳፍንት 19-21)፣ እና የባሎች የአመራር ጸጋ ደብዛው እየጠፋ ሚስቶች በተቃራኒው በባሎቻቸው ላይ ሲሰለጥኑና በቤተሰ የነበረው ሥርዓት እየተቃወሰ መምጣቱን ስናይ ላስተዋለ ሰው ልብ የሚሰብርና እስትንፋስ የሚያቆም ሁኔታ ነው። ስለዚህም በመጽሐፈ መሳፍንት 21:25 ላይ "በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፣ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።" የሚለው ቃል እውነተኛ ያደርገዋል። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር በየዘመናቱ የራሱ ቅሬታዎች አልነበሩትም ማለት አይደለም። በሐዋርያት ሥራ 14:17 ላይ እንደምናየው እግዚአብሔር "ራሱን ያለ ምስክር አልተወም።" የሚለው ቃል የታመነና የፀና ቃል ነው!!!

---

106

ይህንን በተመለከት በሰፊው ለማንበብ ከተፈለገ ከዚህ በፊት የጻፍኩትን መጽሐፍ ማንበብ ይቻላል:- አሳየኸኝ በርኸ ገ/ ሥላሴ፥ *ጋብቻና ቤተሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ* (ሎስ ኤንጀልስ፥ ካሊፎርኒያ፣ ደልታ ፓብሊኬሽንስ፥ 2008).

3. ሦስተኛውና የመጨረሻው ትውልድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ነች። በአዲስ ኪዳን የነበረውን የጋብቻና ቤተሰብ ገፅታ ከማየታችን በፊት፣ አንዳንድ ልናስተውላቸው የሚገቡን እውነቶች መግለፅ አስፈላጊ ነው።

- ❖ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሆኖ እያለ፥ ሰው ሆኖ የእኛን ሥጋ ለብሶ መመጣቱ የተከሰተው የጌታ እናት በሆነችው ማርያምና በዮሴፍ መሃል በቤተሰብ ውስጥ መሆኑን፣
- ❖ ኢየሱስ በምድር ላይ እንደ እኛ ሰው ሆኖ የተመላለሰባቸው ዓመታት ሰላሣ ሦስት ዓመት ተኩል ሲሆን፣ በአገልግሎት ላይ ያሳለፈባቸው ዓመታት ሦስት ዓመት ተኩል ብቻ ነው። የሚበዙት ዓመታት፣ ማለትም ለሰላሣ ዓመታት ያህል ቤተሰቡን ሲያገለግል መቆየቱን፣
- ❖ ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር የአገልግሎቱ እፍታ የሆነውን የመጀመሪያውን ተአምር በቃና ዘገሊላ በሠርግ በቤተሰብ መሃል መፈፀሙን፣ (ዮሐ. 2:1-11)
- ❖ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ እንኳ ስለ እናቱ ሲያስብና ሲጠነቀቅላት ስናይ ፣ ምን ያህል ለቤተሰቡ የተሰጠ እንደሆነ ልናስተውል እንችላለን። (ዮሐ. 19:26-27)
- ❖ ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን አካል እንደ ቤተሰብ በመግለፅ "....የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።" ማለቱን፣ ( ኤፌ. 2:19-22)
- ❖ "ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ስያሜ "በክርስቶስ አምነው የዳኑ ቤተሰቦች ስብስብ " መሆኑን የሚገልፅ የክርስቶስ አካል መግለጫ ማስመልከቱን፣
- ❖ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ. 5:27-32፣7:24:27፣19:1-12)፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ (1ጴጥ. 3:1-7)፣ እና ሐዋርያው ጳውሎስም (1ቆሮ. 5-7፣ ኤፌ. 5:21-6:4 ፣ ቆላ. 3:18-25) ሰፊ ቦታ ሰጥተው ስለ ጋብቻና ቤተሰብ ማስተማራቸውን፣
- ❖ የመደምደሚያ መጽሐፍ የሆነው የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ እንደሚገልፀው ሙሽራ ሆኖ በሚመጣው ጌታ ኢየሱስና ሙሽሪት ሆና በምትጥብቀው በቤተ ክርስቲያን መሃል መግለጫ የሌለው፥ አዕምሮን ሁሉ የሚያልፍና፥ አስደናቂና ክቡር ሠርግ የሚደመደም መሆኑን ስናይ፣ ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዳለው:-

*"የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብን፤ እውቀትም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፤ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም። የጌታን ልብ ያወቀው ማን*

*ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"* (ሮሜ 11፡33-36) እንላለን!!!

## ሐ. የጋብቻና ቤተሰብ ሥነ መለኮት:-

### 1. የዘፍጥረት ምዕራፍ 1-3 ሥነ መለኮት:-

"በመጀመሪያ እግዚአብሔር" (ዘፍ.1፡1) የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገልጹት ታሪኮች ከፋች ከመሆኑም ሌላ ወሳኝ የሆነ ቃል ነው። እነዚህ ሁሉ መጻሕፍት ዋና መልዕክታቸው ስለ ሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩ ናቸው። (ሉቃስ 24፡27፤ ዮሐ. 5፡39) ጌታ ኢየሱስ ራሱ "*መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና*" (ዮሐ፥ 10፡ 35) ብሏል። ኢየሱስም በዘፍጥረት 2፡24 ላይ የተገለፀውን ሐሳብ እንዳለ በመጥቀስ የተናገረው ቃል አሁንም የፀና ነው። "*ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም:- 'ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።'*" (ማቴ. 19፡4-6)

<u>እነዚህ የመከፈቻ ቃሎች በመንፈስ ቅዱስ የተሰጡ፤ ብዙ እውነት የታጨቀባቸውና የእግዚአብሔር ሥልጣን የሞላባቸው እንደሆኑ ልንገነዘብ ይገባል።</u> <u>በሌላ በኩል ደግሞ የማይገባ የተለጠጠና በክፍሉ ሐሳብ ውስጥ ያልተባለ አጉል መንፈሳዊነት (ALLEGORIZATION) ከመስጠትና "ስውር ትርጉም" (HIDDEN MEANING) ለማውጣት ከመሞከር ልንቆጠብ ይገባል።</u> አንድ እርግጠኛ ሆነን ማለት የምንችለው ነገር ለክርስቶስ "የእግዚአብሔር ቃል ተናገረ ማለት፥ እግዚአብሔር ተናገረ ነው።"[107]

"ጌታችን አምላካችን ሆይ፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና፤ ተፈጥረውማልና፤ ክብር፤ ውዳሴ፤ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል።" (ራዕይ 4፡11) የሚታየውና የማይታየው ፍጥረት ሁሉ የፈጠረው እግዚአብሔር ራሱ ነው። እግዚአ

---

[107] B. B. Warfield, *The Inspiration and Authority of the Bible*, (Philadelphia, PA: PRPC, 1948), 299-348.

ብሔር ብቻውን የአህዛብ አማልክት ምንም ነገር ለማድረግ ኃይልና ሥልጣን ካልነበ ራቸው አማልክት ተነፃፃሪ ሆኖ የቆመ እውነተኛና ብቻውን የሆነ አምላክ ነው::[108]

"ፈጠረ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ - ("BARA") በጣም የጠነከረ ክብደት ያለው ትርጉም ይሰጠዋል:: እንዲያውም በብሉይ ኪዳን ብዙ ቦታ ሲጠቀስ አናየውም፤ ከተ ጠቀሰ ደግሞ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከምንም ነገር የሚያስደንቁ፤ እፁብ ድንቅ የሆኑ ፍጥረታትን መፍጠሩን፤ እንዲኖሩ ማድረጉን ለመግለፅ ብቻ ነው:: (ዘፀ. 34:10፤ መዝ. 51:10፤ 104:30፤ ኢሳ. 48:7፤ 65:17፤ ኤር. 31:22) "በመጀመ ሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ::" (ዘፍ. 1:1) "ይሁን አለ፤...ሆነም::" (ዘፍ. 1:2፤6፤9፤14፤20፤26-27)

በዚህ ጉዳይ ላይ ከቀድሞ የሪፎርሜሽን አባቶች መካከል ካልቪን በሰጠው ሐሳ ብ "ምድረም ባዶ ነበረች፤ አንዳችም አልነበረባትም" ከሚለው ቃል ጋር በማያያዝ፤ "ሠራ፤ ቀረፀ፤ አበጀ" (በዕብራስጥ "YATSAR") የሚለው ቃል ሳይሆን የተጠቀመው ፤ "ፈጠረ" (በዕብራይስጥ "BARA") የሚለው ቃል ስለተጠቀመ "ከምንም ነገር አን ዳች ነገር ነው የፈጠረው" ብሎ ያምናል::"[109]

("CREATION OUT OF NOTHING" "EX- NIHILO")[110] እንዲህ ከሆነ "ምድርም <u>ባዶ ነበረች፤ አንዳችም አልነበረባትም</u>፤" የሚለው ቃል (በዕብራይስጥ "ቶሁ" እና "ቦሁ" ("TOHU AND BOHU") እንዴት እንረዳዋለን?

"ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ "ጨለማ የሚያመለክተው "ክፉ" እንደነበረ ነው:: ስለዚህ ይህ "ባዶነት አንዳች አልነበረም" የሚለው ሐሳብ መልካሙን የእግዚአብሔ ርን ፍጥረት ለማበላሸት ከክፉ የመነጨ ክፋት እንደነበረ የሚያመለክት ይመስላል:: የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ከመካድ የተነሳ "ክፉ" እንደነበረ የሚያሳይ ነጸብራቅ ነው:: "እግዚአብሔርና÷ ምንም ነገር!" ("GOD AND NOTHINGNESS")[111]

በሌላ በኩል ቮን ራድ የሚባለው ግን "ውካታና ግዙፉ የፍጥረት ስብስብ" ብሎ ይገ

---

[108] See H. and H. A. Franfurt, *Before Philosophy*, (Penguin, 1963), 237ff.

[109] John Calvin, trans. by John King, *Commentaries on The First Book of moses Called Genesis,* vol. I, (Grand Rapids, MI; Baker Books, 2009), 70.

[110] See Von G. Rad, *Genesis*, (London: SCM, 1963), 47.

[111] Karl Barth, CD III, 1, *The Doctrine of Creation,* (Edinburgh: T & T Clark, 1958), 101-110.

ልፀዋል::[112] የእርሱ ምክኒያት እግዚአብሔር ብቻ ነው:: "ቅርፅ" እና "መሆን" የሚ ሰጥ የሚል መሠረታዊ ሐሳብ ስለሚያምን ነው::

እግዚአብሔር ሥራውን በሚሠረበት ጊዜ መንፈሱንና ቃሉን ተጠቅሟል:: ስለ ዚህም ነው "<u>በመጀመሪያ እግዚአብሔር</u>..." (ዘፍ.1:1) የሚለው:: ሙሴ ይህንን የመጀመሪያውን መጽሐፍ በሚጽፍበት ጊዜ "እግዚአብሔር" የሚለው የእግዚአብሔ ር ስም "ኤሎሂም" የሚለው የብዜት ወይም የክብር ስም ተጠቅሟል:: ምክኒያቱም እግዚአብሔር የፈጣሪነት ሥራውን ያከናወነው በሦስቱ ስብዕናው፣ ማለትም እግዚአ ብሔር አብ፣ ግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክነቱ ነው:: "እግዚአብሔር" (አብ)÷ "ይሁን አለ" የሚለው ቃል (ወልድ)÷ እና "የእግዚአ ብሔርም መንፈስ" (መንፈስ ቅዱስ) (በዕብራይስጥ "ሩአኽ ሎሂም" :- "የእግዚአብ ሔር መንፈስ" (ዘፍ. 1:1-2 ምሳሌ 8:22-31፣ መዝ. 33:6)[113]

እንዲያውም ካልቪን "የእግዚአብሔር መንፈስ" (ዘፍ. 1:2) መጠቀሱን አስመል ክቶ "ዓለም ... የተበታተነ ክፍት ስለነበረ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳይበታተን ለማቆየት እጅግ ያስፈልግ ነበር::" ይላል::[114] እግዚአብሔር ሌሎች ፍጥረታትን ከፈጠረና ለሰው የሚያስፈልፈውን ነገር ካዘጋጀ በኋላ፣ በስድስተኛው ቀን ሰውን ፈጥሯል:: "እግዚአብሔርም አለ:- ሰውን በመልካችን፣ እንደምሳሌአችን እንፍጠር:: ... እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው:: ወን ድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው::" (ዘፍ. 1:26-27) ሰው መልአክም አይደለም፣ ወይን ም አውሬም አይደለም:: "በእግዚአብሔር አምሳል" የተፈጠረ ልዩ ፍጡር ነው:: "በእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው ሐሳብ ግን የተለያዩ ትርጉሞች የተሰጡት እንዳ ሉ መጥቀሱ አስፈላጊ ነው:: አንደኛው:- "መንፈሳዊነታችንን" ነው የሚያሳየው የሚሉ አሉ:: ሁለተኛው:- "ዓለማትን ከመግዛት" ጋር ያገናኙትና በዚህ ይተረጉሙ ታል:: ሦስተኛ:- ሉተር "በመልካችን" እና "በምሳሌአችን" በሚሉት ሐሳቦች መሃል ልዩነት እንዳላቸው ለመቀበል ላለመፈለጉም በተጨማሪ፣ "ነባራዊ ፅድቅ"፣ የሞራል ልቀት"፣ "በኃጢአት ምክኒያት ጠፍቶ የነበረው የእግዚአብሔር ምስያ" ብሎ ይተረ ጉመዋል::[115] የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በሙሉ በዚህ አተረጓጎም ይጠለላሉ

---

[112] Von Rad, *Genesis,* 49.
[113] D. Bonhoeffer, *Creation and Fall,* (London: SCM, 1959), 18.
[114] Calvin, *Genesis,* vol.I, 74.
[115] G. C. Berkouwer, *Man: The Image of God,* (Grand Rapids, MI: Eerdmans Publishing House, 1962), 110f.

::"[116] አራተኛ:- ካርል ባርዝ ደግሞ "በእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው ሐሳብ "የሰው *ፆታነት*" ("HUMAN SEXUALITY)[117] ነው ይለዋል:: ወንድ ያለ ሴት፣ ሴትም ያለ ወንድ መኖር አይችሉም ከሚለው ሐሳብ በመነሣት ነው ይህንን ትርጉም ለመስጠት የቻለው::

ይህንን ሐሳብ ለማጠቃለል መጠቀስ ያለበት ዋና ነገር አለ:: ከሌሎች ፍጥረታት በሙሉ በተለየ ሁኔታ ሰው ብቻ ነው "በእግዚአብሔር መልክ" እና "በእግዚአብሔር ምሳሌ" የተፈጠረው! "*የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፣ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን ታስበው ዘንድ ሰው መንድር ነው ትጎበኘውም ዘንድ የሰ ልጅ ምንድር ነው? ከመላዕክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፣ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው፣ በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁሉንም ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት::*" (መዝ. 8:3-6) ሰው እንደ "ሐውልት ምስል" የእግዚአብሔር ምስል ሆኖ የተሠራ ሳይሆን፣ "በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ" የተፈጠረ ልዩ ፍጡር ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስም "*ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክቡር ስለሆነ...*" (1ቆሮ. 11:7) ይለዋል:: በ2ቆሮ. 3:18 ደግሞ "*ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን::*" ይላል::" ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው::" (ዘፍ. 1:27) የሚለው ሐሳብ የፆታቸው ልዩነት ከመግለፁም ሌላ፣ የስብዕናቸው ልዩነትንም ያሳያል:: ወንድና ሴት ሁለቱም እግዚአብሔር ባዘጋጀላቸው ዕዳሎት እኩልነት እንዳላቸው ያመለክታል:: ወንድና ሴት ለየብቻቸውም ሆነ፣ በአንድነትም "በእግዚአብሔር አምሳል/ ምሳሌ" የሚፈጠሩትን ልጆችን ለመውለድም ከእግዚአብሔር የተሠጣቸው ዕዳሎትና ኃላፊነትም ነው:: (ዘፍ. 4:1፣ 5:1-5)

እዚህ ላይ ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ ግን አዳምና ሔዋን በኃጢአት ላይ ከወደቁ በኋላ "የእግዚአብሔር ምስያ ደበዘዘ? ወይንስ "ጠፋ?" የሪፎርሜሽን አባቶች በኃጢአትና ኃጢአት በሚያመጣው ሰበብ የነበራቸው የጠበቀ አቋም ላለማላላት ሲሉ "የእግዚአብሔር ምስያ" በኃጢአት ምክኒያት ፈፅሞ እንደጠፋ ያምኑ ነበር:: ሆኖም ግን ይህንን ሐሳብ ረጋ ብለን በማስተዋል ብናጤነው የሪፎርሜሽን አባቶች የነበራቸውን ቅንዓት ብናደንቀውም፣ በኃጢአት ምክኒያት "የእግዚአብሔር ምሳሌ" ከሰው ፈፅሞ ጠፍቷል ብለን ለማለት የሚያስችለን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የለን

[116] Emil Brunner, *The Christian Doctrine of Creation and Redemption (Dogmatics 2)*, (London: Lutterworth, 1952), 76.
[117] Karl Barth, *The Doctrine of Creation*, 183-206, 211f.

ም:: "የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል::" (ቆላ. 3፡10) እግዚአብሔር ሰውን "በመልኩና በምሳሌው ሲፈጥረው ምንም እንኳን በኃጢአት ምክኒያት ቢደበዝዝም በቋሚነት የሚኖር ነው:: (ዘፍ. 9፡6፣ 1ቆሮ. ቅቅ፡7፣ ያዕቆብ 3፡9፣) ሰው ግን ኃጢአት በሠራ ቁጥር "በራሱ ላይ ምሥክር" ሆኖአል:: በእግዚአብሔር "መልክና ምሳሌ" የተፈጠረበትን ሰው መሆኑን ረግጦ፣ የዚህ ተቃራኒ የሆነ ኑሮ ይኖራል::

"እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔርም መልክ ፈጠረው፡- ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው:: እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው፡- ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፣..." (ዘፍ. 1፡27-28) የሚለው ቃል ውስጥ ብዙ የታጨቁ እውነቶችን የያዘ ነው:: በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ቋሚነትን ያመለክታል:: "ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" የሚለ ው ጋብቻ በወንድና በሴት መሃል የሚደረግ ክቡር የግንኙነት ሥምረት/ ጥምረት እንጂ፣ ከዚህ የተለየ፣ ያነሰ፣ ወይንም የጎደለው በተመሣሣይ ፆታ የሚደረግ አይደለ ም::ወንድና ሴት በጋብቻ በሚጣመሩበት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን ሰብዓ ዊ እኩልነት የሚያሳይ ሆኖ፣ ቤተሰባቸውን በመምራት ደግሞ የተለያየ ድርሻ እንዳ ላቸው ያመለክታል:: እግዚአብሔር ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ "እንደ ወገናቸው" (ዘፍ. 1፡21-24-25) ("ACCORDING TO THEIR SPECIES") እንደፈጠራቸው ስናይ፣ ሰውን ግን "በመልኩና በምሳሌው" ነው የፈጠረው:: ከዚህም ሌላ ሰው የፍጥ ረት ሁሉ ቁንጮ አድርጎ ስለፈጠረው "ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም" ሲላቸው እናያለን:: "ወንድና ሴት" ከጋብቻ ጥምረት በኋላ ልጆችን መውለዳቸው ትውልድን የማሳደግ፣ የመቅረፅና ቀጣይነት እንዲኖረው የማድረግ ዕዳሎትም ሆነ ኃላፊነት እንዳላቸው ያመለክታል::

## 2. የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት፡-

እስካሁን እንደተመለከትነው ጋብቻ እግዚአብሔር በመለኮታዊ አሠራሩ በፍጥ ረት ጊዜ የመሠረተው እንደሆነ አይተናል:: በአንጻሩም ከውድቀት በኋላ ኃጢአት የጋብቻን መለኮታዊ አሠራር የሚጻረርና እንዲያውም የሚበክል (Marred) እንደሆ ነና በቤተሰቦች መካከል የነበረው ሕብረት በብዙ ውጣ ውረድ ሲያልፍና ባሎችም በሚስቶቻቸው ላይ ለመሠልጠን፥ ሚስቶችም በባሎቻቸው ላይ ለመሰልጠን ሲታገ ሉ የምናየው ትዕይንት ሲቀጥል ነው:: ከዚህም ሌላ ፍቺ በጣም ቀላል በሆኑ ጉዳዮች

ምክንያት ሲከናወን፤ ከአንዷ የቃል ኪዳን ሚስት በላይ ሌሎችን ሴቶች ማግባት መደረግ እንዳለበት ሆኖ ሲቆጠር፤ ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት/ ሴቶች ጋር ዝሙት መፈጸምም ሲቀጥል በመቆየቱ፤ የነበረውም መለኪያ ደብዛው እየጠፋ በመሄዱ ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣበት ዘመን እንደገና መታደስና መሠራት እንዳስፈለገው ልንገነዘብ እንችላለን።

ከዚህ ቀጥሎ በአዲስ ኪዳን ዘመን የጌታ ኢየሱስ አመለካከት፥ የጴጥሮስና፥ የጳውሎስ ትምህርቶች፥ በአጠቃላይም ጋብቻ በአዲስ ኪዳን እይታ ምን ይመስል እንደ ነበር እንዳስሳለን።

## 2.1. የጌታ ኢየሱስ አመለካከት፥

እግዚአብሔር ብዙ ስሞች እንዳሉት ብናውቅም ሁለት የክብር ስሞች አሉት። የመጀመሪያው ስሙ "*ኤል*" (EL) ወይንም "*ኤሎሂም*" (ELOHIM) የሚለው ስም ሲሆን፤ "*ኤል*" የነጠላ ቁጥር ሆኖ፥ "*ኤሎሂም*" ደግሞ የብዜት/ የክብር ስያሜ ነው። "*ኤል*" "*ኤሎሂም*" ማለት "ከፍጥረቱ እጅግ የላቀና ከአዕምሮ በላይ የሆነ እስ ደናቂ አምላክ (Transcendent)፥ ታላቅ፥የሚያስፈራ፥ ሊታይ በማይችል ብርሃን ውስጥ የሚኖር፥ ክቡር፥ ኃያል አምላክ" ማለት ነው። በዘፀአት 6:3 ላይ እንደምናየ ው ለአባቶች ማለትም ለአብርሃም ለይስሃቅና ለያዕቆብ የተገለጠው በዚህ ስም ነው። ሁለተኛው የእግዚአብሔር የክብር ስሙ ደግሞ "*ያህዌ*" የሚለው ስም ሲሆን፤ <u>(YAHWEH -YHWH)</u> (ዘፀ. 3፡ 13-14) ትርጓሜውም "የሩቅ አምላክ ሳይሆን የቅር ብ አምላክ፥ በሕዝቡ መካከልና በሕዝቡ መከራ ውስጥ አብሮ ገብቶ ሕዝቡን ከመከ ራ የሚያወጣ፥ ርኅሩህ፥ አፍቃሪ አምላክ" ማለት ነው። "*ያህዌ*" የሚለው ስም "*<u>አማኑኤል</u>*" ከሚለው ስም ጋር አብሮ የሚሄድና ትርጓሜውም "*<u>እግዚአብሔር ከእኛ ጋር</u>*" ማለት ነው። (ኢሳ. 8፡ 8-10፤ 9፡ 6፤ ማቴ. 1፡ 21-23)

ይህን እላይ የጠቀስነውን ሥነ መለኮታዊ ሐሳብ ማለትም አምላክ እንደ እኛ ሥጋን መልበሱን (The Incarnation of Christ) (ፊል. 2፡ 5-11) በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተፈጸመ ማጤን ይኖርብናል።

- ጌታ ኢየሱስ ከሰው አዕምሮ በላይ በሆነ መንገድ ወንድ ሳታውቅ በመንፈስ ቅዱ ስ ከድንግል ማርያም መፀነሱና በአንድ ቤተሰብ መሃል፥ ማለትም በድንግል ማርያምና በዮሴፍ መሃል መወለዱን ስንመለከት ድንገት የተፈፀመ ታሪክ ሳይሆ

ን፤ ሆነ ተብሎ በዓላማ የቤተሰብን ክቡርነት ለመግለፅ የተፈፀመ አስደናቂ የታሪክ እውነት ነበር።

- ከዚህም በላይ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ከኖረባቸው ዘመናት ከ33 1/2 ዓመታት መካከል 30 ዓመታት በሙሉ ያሳለፈው በቤተሰቡ መሃል መኖሩንና፤ ወላጆቹን ማለትም እናቱን ማርያምንና "አሳዳጊ አባቱ" የነበረው ዮሴፍን በማገልገል ያሳለፈ መሆኑን ስናይ ከአገልግሎት ይልቅ ለቤተሰብ የሰጠው ቦታ ተቀዳሚና ትልቅ እንደነበረ እናስተውላለን። (ሉቃስ 2:41-52)
- በሌላ በኩል መጠቀስ ያለበት ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ካደረጋቸው ተአምራቶች መካከል የመጀመሪያው ተአምር በሠርግ መሃል በቃና ዘገሊላ መፈጸሙን ስናይ አሁንም በድንገት የተደረገ ሳይሆን÷ በዓላማ የተደረገና ለቤተሰብ ያለውን ልዩ አመለካከት ይገልፃል።(ዮሐንስ 2፡ 1-11)

ይህ እንዳለ ሆኖ በማቴ. 19:4-6 ላይ፡- "*እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው÷ አለም÷ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል÷ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል÷ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።*" የሚለው ሐሳብ በዘፍጥረት 2:24 ከተደነገገው የጋብቻ መሠረት ጋር ይስማማል። ጌታ ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥና በሚቀጥሉትም ቁጥሮች (ማቴ. 19:4-12) <u>ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ የሚፈፀም ነው። በኮንትራት የሚገባበት ሳይሆን በቃል ኪዳን የሚተሳሰሩበት የከበረ ግንኙነት ከመሆኑም በላይ፤ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ የተቀራኙበት ቋሚና የዕድሜ ልክ የግኑኝነት ሥምረት ነው</u>። በትዳር ዓለም ውስጥእያሉየሚፈፀሙ ኃጢአቶችም እንኳን ሳይቀር ሰው ሊወጣበት የማይችልበት አዘቅት ውስጥ ካልገባና ለመለወጥ ተስፋ የሌለው በሚሆንበት ጊዜ "*ያለዝሙት ምክንያት*" (በግሪክ ***Porneoia***) ማለትም (Sexual immorality) (ማቴ. 19፡ 9፤ 1ቆሮ6፡ 15-16)ካልሆነ በስተቀር ሊበጠስ የማይችልና የማይገባ የቃል ኪዳን ገመድ መሆኑን በትምህርቱ ገልጾታል። (በተጨማሪም ከብሉይ ኪዳንም የሚከተሉትን ማየት ይቻላል÷ መክብብ 4፡ 12፤ መኃ. መኃ 8፡ 7)

**2.2. የሐዋርያው ጴጥሮስ ትምህርት፥** (1ጴጥሮስ 3፡ 1-7)

ሐዋርያው ጴጥሮስ ትምህርት የሰጠበት ዐውድ(context) መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ጴጥሮስ ይህንን መልዕክት በሚፅፍበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ ከፍተኛ ስደት ተነስቶ ወደ ተለያዩ አገሮች የተበተኑበትና (1ጴጥ. 1፡ 1-2) የነበራቸውን የቤተሰብም ሆነ የሌሎች መሠረታዊ ነገሮች መለኪያ እንደ እሣት በሚያነጥር ሁኔታ እየተፈተነ ያለበት ጊዜ ነበረ፡፡ (1ጴጥ. 1፡ 6-7፤ 4፡ 12-13) እንዲህ ባለ ዘመን ጴጥሮስ "ስለጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ" ይላቸዋል፡፡ (1ጴጥ. 2፡ 13-17) ለነገሥታት፥ ቁጥር 13፤ ለአለቆች፥ ቁጥር 14፤ በሥራ ቦታም፥ ቁጥር 18 እና በቤተሰባቸው መሃል፥ 3፡ 1 እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩ ያሳስባቸዋል፡፡ ለዚህም እንደ ምሳሌ/ ሞዴል ያቀረበላቸው ጌታ ኢየሱስን ነው፡፡ (2፡ 21-24)

ስለዚህ ጴጥሮስ የጋብቻም ይሁን የቤተሰብ ግንኙነት ሰፋ አድርጎ ባስቀመጠው ዐውድ እንዲያዩት የፈለገ ይመስላል፡፡ በማያምነው ሕብረተሰብ መካከል በምንም ዓይነት መከራ ቢያልፉም/ ቢገደሉም እምነታቸውን አፅንተው መያዝ እንዳለባቸው ሁሉ፤ አማኝ የሆኑ ሚስቶችም አማኝ ባልሆኑ ባሎች መካከልም ቢሆኑም፤ እግዚአብሔርን በመፍራት የሚገለፀውን ንፁህ ኑሮ በመኖርና ለባሎቻቸውም በማይመስልና በማይጥም ሁኔታ እንኳን ሳይቀር በመታዘዝ እንዲኖሩ ያስገነዝባቸዋል፡፡ (1ጴጥ. 3፡3-6)

እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ምንም እንኳን ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲጀምር አማኝ የሆኑ ሚስቶች ለማያምኑ ባሎቻቸው ስለሚገባ አኗኗር እየገለፀ ቢቆይም (ቁ1-3)፤ ከቁጥር 4-7 የገለፃቸውን ሐሳቦች ስናይ ግን በአማኝ ባለትዳሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለፅ መቀጠሉንና የሐሳብ ለውጥና ዕድገት እንዳለ ነው፡፡ <u>ስለዚህ ከጴጥሮስ ትምህርት የምንረዳው ጋብቻ መፈጸምና መከናወን ያለበት ሁለት አማኝ በሆኑና በዳኑ ሰዎች መካከል መፈፀም ያለበት እንደሆነ፥ በጋብቻ ዓለምም የባሕርይ ለውጥ ማስፈለጉን፥ ከውጭው ውበት ይልቅ የውስጥ ውበት እጅግ ማስፈለጉን፥ የባሎችም የማስተዋል ደረጃ ቤታቸውን ለመምራት ወሳኝ መሆኑንና ይህም የማስተዋል ብስለት የሚገኘው በእነርሱ በጌታ ፍርሃት መኖርና የመስጠት መጠንና ማስተዋል በሚሰጠው ጌታ መካከል መጣጣም ሲኖር መሆኑን (1ጴጥ 3፡7፤ 2ጢሞ. 2፡ 7) እንገነዘባለን፡፡</u>